# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

81ኛ ዓመት ቁጥር 266 ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የተመራ ከፍተኛ የልዑካን ቡድን ባሌ ሮቤን ጎበኘ

## • “ ዓለም ስለኢትዮጵያ ያለው አረዳድ ትርክቱ ሊቀየር ይገባል”

**- ኦሊሴጉን ኦባሳንጆ (በአፍሪካ ሕብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ)**

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የተመራ ከፍተኛ የልዑካን ቡድን ባሌ ሮቤን ጎበኘ፡፡

በጉብኝቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ የፌዴራል እና የክልል ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ፣ የዓለም ባንክ የኢትዮጵያ ተወካይ ኡስማን ዲዮን፣የአፍሪካ ሕብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ ኦሉሴጉን አባሳንጆ እና ሌሎችም ተሳታፊ ሆነዋል። የልዑካን ቡድኑ በባሌ ዞን እየተከናወኑ ያሉ የግብርና ሥራዎችን ተዘዋውሮ ተመልክቷል፡፡

በባሌ ዞን፣ ሲናና ወረዳ በሲናና ወረዳ በ3 ሺህ 200 ሄክታር መሬት ላይ በክላስተር የለማውን የስንዴ ሰብል በልዑካን ቡድኑ ተጎብኝቷል። በአጠቃላይም በወረዳ ደረጃ 42 ሺህ 901 ሄክታር መሬት ላይ ስንዴ እየለማ መሆኑ ተነግሯል፡፡

በጠቅላይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል











ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ

# የአፍሪካውያን ጥንታዊ ባህል የሆነው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንቅስቃሴ በዓለም አበረታች ደረጃ ላይ መሆኑ ተገለጸ

- በኢትዮጵያ በበጎ ፈቃድ ተግባራት 7 ቢሊዮን ብር የልማት ሥራ ተከናውኗል

ዋቅሹም ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- ዛሬ በሌሎች የዓለም አገራት እንደ አዲስ የሚቀነቀነው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሥራ ለአፍሪካውያን ጥንታዊ ባህል መሆኑንና አፍሪካ በበጎ ፍቃድ እንቅስቃሴ በዓለም የተሻለ ደረጃ ላይ መሆኗ ተገለጸ፡፡

አራተኛው የዓለም የበጎ ፈቃደኝነት ሪፖርት በተመድ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን አዳራሽ “እኩል እና ሁሉን አቀፍ ማህበራትን መገንባት” በሚል መሪ ቃል በይፋ ተጀምሯል፡፡

በመርሐ ግብሩ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ እንዳሉት፣ የኢትዮጵያ መንግሥት በበጎ ፈቃደኝነት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አሸናፊነቱን ለማስቀጠልና ለበጎ ፈቃደኞች ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ቁርጠኛ ነው።

በዚህም በኢትዮጵያ 21 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ባከናወኗቸው የበጎ ፈቃድ ተግባራት 7 ቢሊዮን ብር የሚገመት የልማት ሥራ መከናወኑን ነው ሚኒስትሯ የተናገሩት።

ዶክተር ኤርጎጌ አክለውም፣የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ከጥንት ጀምሮ በደቡብ አፍሪካ ኡቡንቱ በኢትዮጵያ ደግሞ ደቦ እንዲሁም በሌሎች የአፍሪካ አገራት በተለያየ ስያሜ እየተተገበረ ያለ ጉዳይ መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያውን ዛሬም ድረስ ጉልበታቸውን አዋጥተው

የአፍሪካውያን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ እዩብ ተፈሪ

# ከበካይ ጋዝ ነፃ የኃይል አቅርቦት ላይ የተሰማራው ኩባንያ በኢትዮጵያ ለመስራት ተስማማ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- ከበካይ ጋዝ ልቀት ነፃ የሆነ የኃይል አቅርቦት ላይ የተሰማራው የአውስትራሊያው ኩባንያ በኢትዮጵያ ለመስራት ስምምነት ላይ ደረሰ።

ፎርቴስኩ ፊውቸር ኢንዱስትሪስ /FFI/ የተሰኘው ከበካይ ካርበን ጋዝ ነፃ የሆኑና የአረንጓዴ ልማትን መሰረት ያደረጉ የኃይል አማራጮችን የሚያቀርበው ኩባንያ

ከበካይ ጋዝ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ከ7 ሺህ በላይ መጻሕፍትን ለአብርሆት ቤተ-መጽሐፍት አበረከተ

(ኢ.ፕ.ድ) የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ከተለያዩ ቤተ-እምነቶች ያሰባሰባቸውን ከ7 ሺህ በላይ መጻሕፍትን ለአብርሆት ቤተ-መጽሐፍት አበረከተ። ለአብርሆት ቤተ-መጽሐፍት "ሚሊዮን መጻሕፍት ለሚሊኒየሙ ትውልድ" በሚል መሪ ሃሳብ ለአንድ ወር መጻሕፍትን ለማሰባሰብ የቀረበውን ጥሪ ተከትሎ በርካታ ተቋማትና ግለሰቦች ምላሽ እየሰጡ ነው።

ይህንንም ተከትሎ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ከተለያዩ ቤተ-እምነቶች ያሰባሰባቸውን ከ7 ሺህ በላይ መጻሕፍት ለቤተ-መጽሐፍቱ በዛሬው ዕለት አስረክቧል። የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጠቅላይ ጸሐፊ ቀሲስ ታጋይ ታደለ፤ መጻሕፍቱ ከሰባት ቤተ-እምነቶችና ከአማኞቻቸው የተሰባሰቡ መሆናቸውን በመጥቀስ ለቤተ-መጽሐፍቱ አስረክበዋል። መጻሕፍቱ ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው፣ የፍልስፍና፣ የአስተዳደር፣ በሰላም ግንባታና በአብሮነት ላይ ትኩረት ያደረጉ መሆናቸውንም ጠቅሰዋል። ጉባኤው አሁን ላይ ከ7 ሺህ በላይ ያሰባሰባቸውን መጻሕፍት ማስረከባቸውን ጠቁመዋል።

በቀጣይም ጉባኤው ከሰባቱ ቤተ-እምነቶች ጋር በመተባበር በርካታ ቁጥር ያላቸው መጻሕፍትን አሰባስቦ ለማስረከብ ማቀዱን ጠቅሰው፤ ቤተ-እምነቶችም መጻሕፍት እንዲያሰባስቡ ጥሪ አቅርበዋል። የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤትን ወክለው በመገኘት መጻሕፍቱን የተረከቡት ዶክተር ታምራት ኃይሌ፤ ጉባኤው ለአብርሆት ቤተ-መጽሐፍት ላደረገው ድጋፍ አመስግነዋል። "ቤተ-እምነቶች የእውቀት ማምረቻ፤ የእውቀት ማስተላለፊያ ናቸው።" ያሉት ዶክተር ታምራት በቀጣይ ለማሰባሰብ ያቀዷቸውን መጻሕፍት እንዲያሳኩም አበረታተዋል። በርካታ ተቋማት ለአብርሆት ቤተ-መጻሕፍት የመጻሕፍት ድጋፍ እያደረጉ መሆኑን ጠቁመው፤ አጠናክረው



እንዲቀጥሉም ጠይቀዋል።

የመገናኛ ብዙሃንም ለቤተ-መጽሐፍቱ የሕዝብ ድጋፍ እንዳይለይ እያደረጉ ላለው አስተዋጽኦ አመስግነዋል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።



# ለ9 ሺህ 241 መምህራን እና የትምህርት አመራሮች የጽሁፍ ምዘና ተሰጠ

**ዳግማዊት ግርማ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በትላንትናው እለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ 9 ሺህ 241 መምህራን እና የትምህርት አመራሮች በዘጠኝ የመመዘኛ ጣቢያዎች የሙያ ፈቃድ የጽሁፍ ምዘና ተሰጠ። የጽሁፍ ምዘናውም ከ 80 በመቶ የሚያዝ መሆኑን እና ቀሪው 20 በመቶው ደግሞ የማህደረ ተግባር ምዘና ተካሂዶ እንደሚያዝ ተመላክቷል።

ምዘናውን የሚያደርገው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን ምክትል ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ስንታየሁ ማሞ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ዘጠኝ ሺህ 241 መምህራን እና የትምህርት አመራሮች በዘጠኝ የመመዘኛ ጣቢያዎች የሙያ ፈቃድ የጽሁፍ ምዘና ወስደዋል።

የዘንድሮውን ምዘና በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን ቀደም ብሎ መረጃ የማሰባሰብና የህትመት ሥራዎች መሰራታቸውን የገለጹት ወይዘሮ ስንታየሁ፤ በሌሎች ተመዝነው ብቁ የሆኑ መምህራንና የትምህርት አመራሮች በመዛኝነት መሳተፋቸውንም አስታውቀዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ በበኩላቸው ፤ የብቃት ምዘናው የመምህሩንም እና የትምህርት አመራሩን በራስ መተማመን ከማሳደጉ ባሻገር ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችል ሥርዓት መሆኑን አስረድተዋል።

የመምህርነት ሙያ በትውልድም ሆነ በሀገር ግንባታ ሂደት ውስጥ ትልቁን አሻራ በማሳረፍ ላይ የሚገኝ ሙያ መሆኑን ያመላከቱት አቶ ዘላለም፤ ምዘናው መምህራኑ ያሉበትን የብቃት ደረጃ ለማረጋገጥና በሀገርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችል ሥርዓት መሆኑን አመላክተዋል።

የምዘና ሂደቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ በተመዛኝ ቁጥር እያደገ መምጣቱ መምህራኑም ሆኑ የትምህርት አመራሮቹ ለምዘና ሥርዓቱ ያላቸውን ፈቃደኛነት እንደሚያሳይም አቶ ዘላለም ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ድንቅ ዓለም ቶሎሳ በበኩላቸው የሙያ ማህበሩ የምዘና ሂደቱ በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ሲሰራ መቆየቱን ገልጸው ተመዛኝ መምህራኑም በፍቃደኝነት ምዘናውን ለመውሰድ መምጣታቸው የሚደነቅ ተግባር መሆኑን ገልጸዋል።

የሙያ ብቃት ምዘናው በ2004 ዓ.ም ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን በአዲስ አበባ ውስጥ 14 ሺህ የሚሆኑ መምህራንና የትምህርት አመራሮች መመዘናቸውም በወቅቱ የተመላከተ ሲሆን፤ መሰል ምዘናዎች በሀገሪቱ ከሚገኙ ሰባት መቶ ሺህ በላይ መምህራንና የትምህርት አመራሮች ውስጥ ለአምስት መቶ ሺህ በላዩ መሰጠቱም ታውቋል።

# ከተማ አስተዳደሩ

## ደሀ ተኮር ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ መሆኑን አስታወቀ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደሀ ተኮር በሆኑ ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ መሆኑን አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በርካታ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎችን ማዕከል በማድረግ ሥራዎች እያከናወነ መሆኑን የገለጸ ሲሆን በትላንትናው እለት በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ነዋሪዎች ተጠቃሚ የሚያደርግና በኢስት አፍሪካን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር አማካኝነት የሚገነባ የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ ማስጀመሪያ መርሐግብር ይፋ ሆኗል፡፡

በማስጀመሪያ መርሐግብሩ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ ዣንጥራር አባይ ክረምቱ ከመግባቱ በፊት ሰፋፊ ፕሮጀክቶችን ተቀርፀው ወደ ተግባር መግባታቸውንና የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ሰፋ ያለ ቁጥር ያለው ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ወገኖቻችን የሚገኙበት በመሆኑ መንግሥትና የግል ባለሀብቱ በቅንጅት በመሆን የደሀውን ማህበረሰብ ችግሮች ሊቀርፉ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን እየሰራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡




**የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ ዣንጥራር አባይ**

ከፍተኛ የመኖሪያ ችግር ያለባቸው ወገኖችን ተጠቃሚ የሚያደርግ በኢስት አፍሪካን ሆልዲንግስ ኃ/የተ/የግ/ ኩባንያ አማካኝነት በቁጥር ሃምሳ ለሚደርሱ አባወራዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የጋራ መኖሪያ ግንባታ እንደሚከናወን አስታውቀዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር በቀን አንድ ጊዜ በልተው የማይውሉ ወገኖቻችንን ሊመግብ የሚችል የምገባ ማዕከል በመክፈት የምግብ አገልግሎት እንዲያገኙ የማድረግ ተግባር እየተከናወነ መሆኑን ገልፀው፣ ይህን ተግባርም ለመወጣት የኢትዮጵያ ወጣቶች ዲያስፖራ አባላት ማህበር አማካኝነት በክፍለከተማው ወረዳ አምስት ግንባታው የሚሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በሌላ በኩል ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች ታሳቢ ያደረገ የዳቦ ፋብሪካ በክፍለ ከተማው እንደሚገነባ ምክትል ከንቲባው አረጋግጠዋል፡፡




**ወይዘር ሽታዬ መሀመድ**

የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሮ ሽታዬ መሀመድ በበኩላቸው በክፍለ ከተማው የሚገነቡ ፕሮጀክቶች ማህበረሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ በመሆናቸው በዚህ ግንባታ ላይ ለመሳተፍ ቃል ገብተው ግንባታውን የጀመሩ ባለሀብቶችን አመስግነዋል። ማህበረሰቡም ለሥራው መሣካት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል።

በክፍለ ከተማው ደሀውን ማህበረሰብ የሚያገለግሉ የጋራ መኖሪያ ግንባታዎች፣ የምገባ ማዕከላት እንዲሁም የዳቦ ፋብሪካ ግንባታዎችን በማስጀመር በፍጥነት ለማህበረሰቡ እንዲተላለፍ የሚደረግ መሆኑን ተናግረዋል።

የኢስት አፍሪካን ሆልዲንግስ ኃ/የተ/የግ/ ኩባንያ ተወካዮች በበኩላቸው የማህበረሰቡን ኑሮ ሊያሻሽሉ የሚችሉ ተግባራት ላይ በመሳተፍ ማህበረሰቡ ካለበት አስከፊ የኑሮ ሁኔታ ለማላቀቅ በሚሰራው ተግባር ላይ በመሳተፍ በአጭር ጊዜ ውስጥ ፕሮጀክቶቹን ገንብቶ ለተጠቃሚው እንደሚያስተላልፍ ቃል ገብተዋል፡፡

# ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሀገራት የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብሩን እንዲቀላቀሉ ጥሪ አቀረቡ



አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሀገራት እና አጋር አካላት ኢትዮጵያ የጀመረችውን ለትውልድ የሚተላለፈውን አረንጓዴ አሻራ የማሳረፍ ጉዞ እንዲቀላቀሉ ጥሪ አቀረቡ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ስዊድን እና ኬንያ በጋራ ስቶኮልም ፕላስ 50 የተሠኘውን ኮንፈረንስ በማዘጋጀታቸው አድናቆታቸውን ገልጸዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለኮንፍረንሱ በቪዲዮ ባስተላለፉት መልዕክት የስቶኮልም ኮንፈረንስ ልማትን ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ያወዳጀ የመጀመሪያው ኮንፈረንስ እንደሆነ አንስተዋል።

በኮንፈረንሱ ድህነትን በተመለከተ የተነሱ ሃሳቦች ቦታ ተሰጥቷቸው መንሸራሸራቸውንም አድንቀዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ሀገራት ከተፈጥሮ ጋር ያላቸው መስተጋብር አካባቢን በማይጎዳ እና ዓለም አቀፉን የአካባቢ ጥበቃ ሥምምነት መርሆዎች ባከበረ መልኩ መሆን እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

ጤናማ ዓለም እንዲኖረን ተባብረን በአንድነት በመቆም መሥራት ግድ ይለናልም ነው ያሉት፡፡

እያጋጠሙን ያሉትን ፈተናዎች ለመፍታት በበኩላችን ምን ተወጥተናል ? በቀጣይስ በሀገር እና በተቋም ደረጃ የአካባቢ ጥበቃ ላይ ለመሥራት ምን አስበናል ? በሚሉት ጉዳዮች ላይ መሥራት ይኖርብናል ነው ያሉት።

ዓለም አቀፉን የአካባቢ ጥበቃ ሥምምነት መርሆዎችንም አክብረን ለተግባራዊነቱ መሥራት እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ በአካባቢ ጥበቃ ላይ በርካታ ሥራዎች መሥራቷንና አሁንም እየሠራች እንደምትገኝ ያነሱ ሲሆን፣ ለአብነትም በፈረንጆቹ 2019 ተግባራዊ መደረግ የተጀመረውን የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብርን ጠቅሰዋል።

በመርሐ-ግብሩ እስከ ፈረንጆቹ 2022 ድረስ 20 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ ከዕቅድ በላይ ማሳካት መቻሉን አንስተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እስከ በፈረንጆቹ 2021 ድረስ 18 ቢሊዮን ችግኞች መትከል እንደተቻለ ያነሱ ሲሆን፣ በዚህ ዓመት ችግኖችን መትከል ስንጀምር ደግሞ በአራት ዓመታት ውስጥ እናሳካለን ብለን ካቀድነው በላይ ችግኞች ከወዲሁ መትከል እንችላለን ብለዋል፡፡

ይህ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ችግኖችን በመትከል የተወሰነ ሳይሆን ከሀገራት ጋር በመተባበር፣ በጋራ በመቆምና ፣ ችግኞችን በመካፈል ሌሎችም ተክለው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር ተካፋይ እንዲሆኑ ያስቻለ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

በቀጣይም ሀገራት የአካባቢ ጥበቃ እና የዓለማችንን ጤንነት ከመጠበቅ አንጻር ኃላፊነት ወስደው እንዲተገብሩ ኢትዮጵያ በጀመረችው የአረንጓዴው አሻራ የልማት ጉዞ ላይ ተካፋይ እንዲሆኑ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለ መተባበር እና በአንድነት ስለመቆም ያነሱትን ሃሳብ ሲያብራሩም፣ ሁላችንም የአንድ ዓለም ህዝቦች እንደመሆናችን መጠን የሚከሰቱ ችግሮችም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሁላችንንም ያገኙናል ብለዋል፡፡

ለአብነትም የኮቪድ 19 ወረርሽኝ መከሰት ሁላችንንም የፈተነና በአንድነት እና በትብብር እንድንቆም ያስቻለ አጋጣሚ ነው ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቀጣይም ሁሉንም ሀገራት ያካተተ፣ በዕውቀት ሽግግር እና በትምህርት ላይ የተመሠረተ መተጋገዝ ሊኖር እንደሚገባ ማሳሰባቸውን ፋና ዘግቧል፡፡

# ‹‹የኢትዮጵያ ስጦታዎች›› የተሰኘ ዓለም አቀፍ ፌስቲቫል በወዳጅነት ፓርክ ተካሄደ

*ፌስቲቫሉ የሀገርን ገጽታ ግንባታን በማሳደግ ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ እንዲያለሙ ያግዛል*

*- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር*

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ፌስቲቫሉ የሀገራችን መለያ የሆነውን ጤፍን፣ እንጀራና ባህላዊ ምግቦችን መሰረት አድርጎ መዘጋጀቱ ወቅታዊ የገጽታ ግንባታ ሥራ በማሳደግ ኢንቨስተሮች በግብርናው ዘርፍ ኢትዮጵያ ላይ እንዲያለሙ እንደሚያግዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ኖርዲክ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በዓለም አቀፍ ደረጃ በኢትዮጵያ ላይ ያለውን የተዛባ አመለካከት ሊቀርፍ የሚያስችልና የሀገር ገጽታ ግንባታን ለማሳደግ የሚረዳ ያለውን ‹‹የኢትዮጵያ ስጦታዎች›› የተሰኘ ዓለም አቀፍ ፌስቲቫል ትናንትና በወዳጅነት ፓርክ ተካሂዷል።

በመርሐግብሩ ላይ የተገኙት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ እንደገለጹት፤ ጤፍና እንጀራ የኢትዮጵያ መገኛና መገለጫ መሆናቸውን ከመጠቀሚያ ግብአቶችና ከባህላዊ እሴቶች ጋር ለዓለም ከማስተዋወቅ ባሻገር ለሀገራችን ተጨማሪ ኢኮኖሚ አቅም መፍጠር ያስችላል።

በተጨማሪ ኤግዚቢሽኑ ወቅታዊ የገጽታ ግንባታ ሥራውን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል። በተለይ የውጭ ኢንቨስተሮች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ታግዘው በግብርናው ዘርፍ ኢትዮጵያ ላይ እንዲያለሙ የሚያነቃቃ ሥራ ነው ብለዋል።

በቀጣይም ተመሳሳይ አካሄዶችን በመከተል የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ ለውጭ ሀገራት በማስተዋወቅ የገጽታ ግንባታ ሥራ እንደሚሰራ ጠቁመዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ ዝግጅቱ ኢትዮጵያ ያላትን ባህል፣ ቅርስና ቱፊት በዓለም አቀፍ ደረጃ በማስተዋወቅ ገጽታ በመገንባቱ ረገድ የበኩሉን ሚና የሚጫወት በመሆኑ ፋይዳው የጎላ ነው።

ይህ ዓለም አቀፍ ፌስቲቫል የሀገራችን መለያ የሆኑ ባህላዊ ምግቦችና መጠጦችን መሰረት አድርጎ ትውፊታችንን፤ የቡና ስርዓታችንንና እንዲሁም ሌሎች የሀገራችን መለያዎች ላይ በማተኮር በሌሎች አገራት ይከናወናል ብለዋል።

በተለያዩ የአውሮፓ፣ የአሜሪካና የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት የሚካሄድ በመሆኑ ሀገራችንን በዓለም



**አምባሳደር ብርቱካን አያኖ**

አቀፍ ረገድ ጥሩ ገጽታ እንዲኖራት ያደርጋል ሲሉ ተናግረዋል።

የቱሪዝም ሚኒስቴር ዴኤታ አቶ ስለሽ ግርማ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ያላትን ሀብት ወደ ኢኮኖሚ ለመቀየርና የሀገራችንን ገጽታ ለመገንባት ቱሪዝም ሚኒስቴር በርካታ ሥራዎችን እየከወነ ይገኛል።

ከለውጡ ማግስት ጀምሮ መንግሥት በቱሪዝሙ ዘርፍ ከፍተኛ የሆነ ትኩረት በመስጠት ለውጥ አምጥቷል፤ ቱሪዝም ምጣኔ ሀብታዊ አቅሙ ታውቆ ቀድሞ ከነበረበት የማህበራዊ ዘርፍ ወጥቶ በኢኮኖሚ ዘርፍ እንዲጠቃለል በመደረጉ ለውጥ ተገኝቷል ሲሉ ገልጸዋል።

ለቱሪዝም ዘርፉ ከተሰጡት ትኩረቶች ውስጥ ለማሳያነትም ራሱን ችሎ በሚኒስቴር ደረጃ እንዲደራጅ ተደርጓል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ባለፉት ጊዜያት የቱሪዝሙን ዘርፍ ለማልማት ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖርም የቱሪዝም መዳረሻዎችን ማልማት የተጀመረው ከለውጡ በኋላ መሆኑን ጠቁመዋል።

የቱሪዝሙ ዘርፍ ከሌሎች ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ እንዲሰራና የግሉን ዘር እንዲደግፍ በማድረግ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝም አስገንዝበዋል።

‹‹የኢትዮጵያ ስጦታዎች›› የተሰኘው ዓለም አቀፍ ፌስቲቫል በአውሮፓ፣ በአሜሪካና በተለያዩ የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት በቀጣይ እንደሚካሄድ ይጠበቃል።



# የትናንት ህጸጾችን ለቅሞ ማረምና ዛሬን ከትናንት የተሻለ ማድረግ ይገባል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የትናንት ህጸጾችን ለቅሞ ማረምና ዛሬን ከትናንት የተሻለ ለማድረግ በትኩረት መስራት እንደሚገባ ተገለጸ።

በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ አዘጋጅነት “የብዝሃ-ባህል አገር አቀፍ ተግዳሮቶች፣ አገራዊ መግባባትና የታሪክ ትምህርት ሚና በኢትዮጵያ አንዳንድ ምልከታዎች›› በሚል ርዕስ ትናንት ውይይት ተደርጓል።

በውይይት መድረኩ ላይ የመነሻ ጹሁፍ ያቀረቡት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህርና ተመራማሪው ግርማ ነጋሽ (ዶክተር) እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በፖለቲካል ታሪክ ላይ የተመሰረቱ ቅራኔዎች አስተናግዳለች፣ እያስተናገደችም ነው። በተለይ ያለፈ ታሪክን ለግጭት መነሻ በማድረግ ባኮረፉ ቁጥር የጋራ ታሪክ የለንም የሚለው ፖለቲካዊ ታሪክ መታረም እንዳለበት አመላክተዋል።

ግርማ (ዶክተር) በመነሻ ጹፋቸው በአገራዊ ምክክሩ የታሪክ ሚና ምን መሆን አለበት?፣ የቱ ነው እውነተኛ ታሪክ?፣ ብዝሃነት በሞላበት ውስጥ ታሪክ የሚጠናበት አግባብ እንዴት ቢሆን ይሻላል? ለመሆኑ መጥፎና ጥሩ ታሩክ አለን? ለልጆቻችን ማስተማር ያለብን የትኛውን ታሪክ ነው? በሚሉ ጉዳዮች ላይ በማተኮር የተለያዩ የታሪክ ድርሳናትን በማጣቀስ አቅርበዋል።

እንደ አገር ለታሰበው አገራዊ ምክክር ግብ እንዲመታ በታሪክ ላይ ያሉ እይታዎችን በምክንያትና በማስረጃ በማቅረብ የነበሩ ክፍተቶችን በማረም የሚያግባባ አገራዊ ታሪክ ላይ በመመስረት የብዝሃ ባህል፣ ታሪክ ያላትን አገር ማስቀጠል ይገባል።

አሁን እየታየ ያለው አገራዊ ችግር ከአያያዝ የመጣ ችግር እንጂ ብዝሃነት በራሱ ችግር አይደለም። በታሪክ ትምህርት ታሪክን ለልጆቻችን የምናስተምርበት ሂደት መቃኘትና መታረም ይገባዋል ብለዋል።

በአፍሪካ ናይጀሪያ ከ200 በላይ ፣ ኮንጎ ከ250 በላይ፣ ኬንያ ከ100 በላይ ብዝሃ ባህል ያላቸው ጎሳዎች ያሏቸው ሲሆን ብዝሃነታቸውን ወደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በሰላም እየኖሩ ነው።

በኢትዮጵያም ፖለቲካ ወለድ የሆነው ታሪክ ለግጭት የሚዳረግበትን መንገድ በመቅረፍ አስታርቆ እንደ አገር አንድ የሚያደርጉ ታሪኮችን በመጠቀም ወደ መልካም አጋጣሚ መለወጥ ያስፈልጋል። የታሪክና የአገር ግንባታን በብዝሃነት ጽንሰ ሀሳብ አጣጥሞ መጠቀም ተገቢ መሆኑን ግርማ (ዶክተር) አመላክተዋል።

የጋራ ታሪክ የለንም ለሚሉት ከማይጨው እስከ አድዋ፣ በህዳሴው ግድብ፣ በአንድነት የመቆም፣ የጋብቻ፣ የመጋራት፣ የንግድ፣ የካራማራ ድል፣ የሶማሌ ጦርነት አንድ የሚያደርጉ በርካታ ታሪኮች እንዳሉን አብነት አንስተዋል።

እንደ አንድ ፖለቲካዊ ማህበረሰብ ለመቀጠል የሚያስፈልጉ የጋራ ታሪኮች ላይ በትኩረት መስራት፣ በታሪክ ለግጭት ከመንደርደር ይልቅ ለአብሮነት የሚጠቅመውን አጉልቶ በማውጣት መስራት ይገባል። ታሪክን ለዛሬና ለነገ ያለውን ፋይዳ መለካት አስፈላጊ ነው። በማይጨበጡ የትንተና ወጎች እየተጋጩ መኖር ሊቆም ይገባል። የትናንት ህጸጾችን ለቅሞ ማረምና ዛሬን ከትናንት የተሻለ ማድረግ ከታሪክ የሚገኝ ትልቅ ጸጋ ነው።

ከመበታተን አደጋ ለመትረፍ ታሪክን እንደ ሙጫ መጠቀም ያስፈልጋል ያሉት የታሪክ ምሁሩ፤ መንግሥት የጋራ የሆኑ ታሪኮች የህዝብን አንድነት እንዲያጎለብቱ ሊሰራ ይገባል። ብዝሀነት የኢትዮጵያ ዋና መገለጫ ነው፣ አገራዊ ዕሴቶችን ማስረጽ ያስፈልጋል። ታሪክን እንደ ማስተሳሰሪያ ሙጫ መጠቀም አስፈላጊ ነው።

ተሳታፊ ምሁራን ታሪክን እንዴት ማስማር፣ ግጭቶችን እንዴት ማስቆምና ለአገራዊ ምክክሩ ውጤታማነት ታሪክን እንዴትና በምን መልኩ መጠቀም እንደሚገባ ሀሳብ ሰጥተዋል።

# 66 ትምህርት ቤቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የዲጂታል ትምህርት ማዕከል ፕሮጀክት ይፋ ሆነ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ቴሌኮም በአገር አቀፍ ደረጃ 66 ትምህርት ቤቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የዲጂታል ትምህርት ማዕከል ፕሮጀክት አስጀመረ፡፡

ኢትዮ ቴሌኮም በአዲስ አበባ ከፍተኛ 23 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዲጂታል ትምህርት ማዕከላት ፕሮጀክት አስጀምሯል፡፡

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ፍሬህይወት ታምሩ በዚሁ ወቅት እንደገለጹት፣ ተቋሙ ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ እየሰራ ነው፡፡

ተማሪዎች በትምህርት ቤቶች ቴክኖሎጂን በማወቅ ቢያድጉ ውጤታማ እንደሚሆኑ ጠቅሰው፣ በዲጂታል ትምህርቱ 140 ሺህ 596 ተማሪዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቱ ተግባራዊ የሚሆነው በክልሎች በ48 ትምህርት ቤቶች እና በአዲስ አበባ ደግሞ በ18 ትምህርት ቤቶች መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ትምህርት ቤቶቹ ከዚህ በፊት የመሠረተ ልማት ችግር ያለባቸው ሲሆኑ፣ በቀጣይ ከኢትዮ ቴሌኮም ስልጠና እንደሚያገኙ ተገልጿል፡፡





## ‹‹ጀርመን አገራዊ የምክክር ሂደቱን ለመደገፍ ዝግጁ ናት››

- አምባሳደር ስቴፋን አወር

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ጥያቄ ከቀረበላት ጀርመን አገራዊ የምክክር ሂደቱን ለመደገፍ ዝግጁ መሆኗን በኢትዮጵያ የጀርመን አምባሳደር ስቴፋን አወር ገለጹ።

አምባሳደር ስቴፋን አወር በኢትዮጵያ የሚስተዋሉትን ውስጣዊ ችግሮች በመፍታት መፍትሔ ለማበጀት በጋራ መምከር እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የምታካሂደው አገራዊ ምክክር ሁሉንም አሳታፊና አካታች ሆኖ ሲካሄድ ልዩነቶችን ተነጋግሮ በመፍታት ብሔራዊ መግባባት መፍጠር እንደሚያስችልም አንስተዋል።

በአገራዊ ምክክሩ ለጋራ ችግሮች መንስኤ የሆኑ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? የሚለውን ቁልፍ ጥያቄ በማንሳትና በግልጽ መነጋገር የጋራ መፍትሔ ማምጣት ይቻላል ያሉት አምባሳደሩ፣ የምክክር ሂደቱን ሁሉን አቀፍ ለማድረግ እየሰራ መሆኑንም አድንቀዋል።

የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር የኢትዮጵያን መሰረታዊ ችግሮች ለመፍታት ጥሩ የመፍትሔ አማራጭ መሆኑን ጠቁመው፣ የፌዴራል ሥርዓት የምትከተለው ጀርመን ከኢትዮጵያ መንግሥት ጥያቄ ከቀረበላት የምክክር ሂደቱን በሚቻለው አቅም ሁሉ ለመደገፍ ዝግጁ እንደሆነች አረጋግጠዋል።

የኢትዮጵያና ጀርመን የሁለትዮሽ ግንኙነት በጠንካራ ወዳጅነት የቀጠለ መሆኑን ያስታወሱት አምባሳደሩ ፣ "ኢትዮጵያ የጀርመን ስትራቴጂካዊ አጋራችን ናት" ሲሉ ተናግረዋል።

በልማት ድጋፍና ትብብር ጀርመን የኢትዮጵያ ዋነኛ አጋር መሆኗን ጠቅሰው፣ ለዚህም የኢትዮጵያን ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት ትሻለች ማለታቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

የጀርመን ባለሃብቶች በአገሪቷ በተለያዩ የልማት ዘርፎች መዋዕለ ነዋያቸውን እያዋሉ መሆኑንም አምባሳደሩ ገልጸዋል።

# ከበካይ ጋዝ ነፃ የኃይል አቅርቦት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ባለቤቶች ከገንዘብ ሚኒስትር አቶ አህመድ ሽዴና ከማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ኡማ ጋር ትናንትና ውይይት አድርገዋል።

ከውይይቱ በኋላ አቶ አህመድ ሽዴ እንደገለጹት፤ ኩባንያው በአረንጓዴ ልማት ላይ መሰረት ያደረጉ የኃይል አማራጮችን በማቅረብ ልምድ ያለው በመሆኑ በኢትዮጵያ ሥራ ለመጀመር መወሰኑ በዘርፉ ትልቅ ለውጥ እንደሚያመጣ ይታመናል።

ኩባንያውን ወደኢትዮጵያ ገብቶ እንዲሰራ ከመስከረም ወር 2013 ዓ.ም አንስቶ በየጊዜው የቀጠለ ውይይት ሲካሄድ እንደቆየ ያስታወሱት ሚኒስትሩ፤ ከበርካታ ምክክሮች በኋላ ኩባንያው ወደሥራ ለመግባት መወሰኑ በኢትዮጵያ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የበኩሉን ሚና እንዲወጣ ዕድል የሚፈጥር ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ያላትን የጸሐይ፣ የነፋስ ፣ የውሃና ሌሎች የተፈጥሮ ሃብቶች ተጠቅማ ከበካይ ጋዝ ነፃ በሆኑ የኃይል አቅርቦቶች ላይ ከኩባንያው ጋር በስፋት ትሰራለች። መንግሥትም ለኩባንያው ሥራ መሳካት ድጋፍ ያደርጋል ሲሉ አስታውቀዋል።

ከግሉ ዘርፍ ጋር በጋራ ተጠቃሚነት ላይ በተመሰረተ አካሄድ የተለያዩ የአረንጓዴ ልማት ኢንቨስትመንቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ ያሉት አቶ አህመድ፤ በዚህም አየር ንብረትን እየጠበቁ፤ የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ በመስራትና



ቴክኖሎጂን በማዘመን ኢትዮጵያን በአረንጓዴ ኃይል አቅርቦት የአፍሪካ ማዕከል ለማድረግ የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የአውስትራሊያ አምባሳደር ጁሊያ ኒብሌቲ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ኩባንያው በኢትዮጵያ ገብቶ በመስራቱ የአየር ንብረት ለውጥን በመከላከል ረገድ ሰፊ ጥቅም የሚሰጥ ሥራ እንደሚያከናውን ይጠበቃል።

ኢትዮጵያ ከበካይ ጋዝ ነፃ የሆነ የኃይል አቅርቦቷን ለማስፋት በምታደርገው ጥረት የኩባንያው መምጣት ተጨማሪ አቅም የሚፈጥር ነው። ኩባንያው በዘርፉ ካለው ትልቅ ልምድና አቅም አንጻር የኢትዮጵያን የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ዕድገት ለማፋጠን ተመራጭ ድርጅት ነው ብለዋል።

የኃይል አቅርቦትን በሚያሰፉ አማራጮች ላይ ተባብሮ መስራት ውጤታማ ያደርጋል ያሉት አምባሳደሯ፤ ኩባንያው ወደኢትዮጵያ ገብቶ እንዲሰራ በሚመለከታቸው ተቋማትና ግለሰቦች ለተደረገላቸው ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል።

ኩባንያው ወደኢትዮጵያ ገብቶ ለመስራት መወሰኑን ባሳወቀበት ስነስርዓት ላይ የማዕድን ሚኒስትሩ ኢንጂነር ታከለ ኡማ፤ የገንዘብ ሚኒስትር ባለሙያዎች፣ የፎርቴስኪይ ፊውቸር ኢንዱስትሪስ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጁሊ ሸትልወርዝና ሌሎች የኩባንያው ሰዎችን ተገኝተዋል።

# በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የጉብኝቱ አካል የሆኑት የቀድሞ የናይጄሪያ ፕሬዚዳንትና በአሁኑ ወቅት የአፍሪካ ሕብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ ሆነው እያገለገሉ ያሉት ኦሉሴጉን ኦባሳንጆ አሁን ላይ በሀገሪቱ የሚሰሩት የልማት ሥራዎች ኢትዮጵያን በተመለከተ ዓለም እየተረዳበት ያለው ሁኔታ ትርክቱ ሊቀየር እንደሚገባ ተናግረዋል።

ኦሊሴጉን ኦባሳንጆ እንዳሉት ፣ "አሁን በሀገሪቱ የግብርና ዘርፍ እየተሠራ ያለው ልማት ኢትዮጵያ ለህዝቧ ብቻ ሳይሆን ለቀጠናው ጭምር ለውጥ ማምጣት የምትችል ሀገር መሆኗን የሚያሳይ ነው" ብለዋል።

ልዩ መልዕክተኛው፤ በኢትዮጵያ ያጋጠመውን ጦርነት ብቻ ሳይሆን እየተሠሩ ያሉ አበረታች የግብርና እንቅስቃሴዎችን መመልከት ችያለሁ፤ መሬት ላይ ያለውን ይህን እውነት ዓለም እንዲገነዘብ በተደጋጋሚ ማስረዳት እና ማሳየት ይገባል ሲሉ ገልፀዋል።

ኦባሳንጆ፤ ዓለም ስለጦርነቱ መዘገብ ብቻ ሳይሆን ለሰላም ዋስትና የሚሆኑ የተሠሩ የልማት ሥራዎችን ጭምር በመመልከት ኢትዮጵያን በዚህ ደረጃ ሊረዳት ይገባል በማለት ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ እያከናወነች የሚገኘው ሥራ አበረታችና ለበርካታ የአፍሪካ ሀገራት ተሞክሮ መሆን የሚችል ተግባር ነው ብለዋል፡፡

የአፍሪካ ሀገራት ለግብርናው ዘርፍ ትኩረት ሰጥተው ከሠሩ የምግብ ዋስትናቸውን ከማረጋገጥ ባሻገር ምርታቸውን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ኢኮኖሚያቸውን ሊያሻሽሉ እንደሚችሉም ገልፀዋል፡፡

የዓለም ባንክ የኢትዮጵያ ተወካይ ኡስማን ዲዮን በበኩላቸው፤ በአፍሪካ በተለያዩ ቦታዎች የተሠሩ የግብርና ልማት ሥራዎችን መጎብኘታቸውን አንስተው በኢትዮጵያ የተሠራው የግብርና ልማት ትልቅ መሆኑን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የያዘችውን መሰል የልማት እንቅስቃሴ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ትልቅ ሚና ስለሚኖረው የዓለም ባንክ ድጋፉን አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል ኃላፊው።

# የአፍሪካውያን ጥንታዊ ባህል የሆነው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለአቅመ ደካሞች ቤት የሚሰሩና የግብርና ሥራን የሚያከናውኑት በደቦና ጅጊ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

በ1970ዎቹ አካባቢ የኢትዮጵያ መንግሥት ማይምነትን ለማጥፋት ብሎም የትምህርት ተደራሽነት ለማረጋገጥ በዘረጋው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሐ ግብር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ከመመረቃቸው በፊት ህዝቡን በነጻ በማስተማር ማይምነትን በአንዴ ከ90 በመቶ ወደ 37 በመቶ ማውረዳቸው በታሪክ የሚወሳ ክስተት መሆኑን ዶክተር ኤርጎጌ አውስተዋል፡፡

ምንም እንኳ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ ባህላዊ እሴት ቢሆንም ተገቢ እውቅና በመስጠት ተቋማዊ ማድረግ ላይ ክፍተት መኖሩን የጠቆሙት ሚኒስትሯ፣ ሀብት፣እውቀትና ጎልበት በማቀናጀት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጥ ለማምጣት የኢትዮጵያ መንግሥት ለጎዳዩ ትኩረት በመስጠት ከ2004 ጀምሮ የወጣቶች በጎ ፍቃድ አገልግሎት ፖሊሲ በማዘጋጀት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በተዘጋጀው አገራዊ የወጣቶች በጎ አገልግሎት ፖሊሲ ማዕቀፍ መሰረት ከ2020 እስከ 2021 ወደ 21 ሚሊዮን የሚጠጉ በጎ ፍቃደኛ ወጣቶች በችግኝ ተከላ፣በቤቶች እድሳት፣ በማጠናከሪያ ትምህርት አገልግሎቶች ላይ በማሰማራት በርካታ ውጤት ማስገኘቱን የገለጹት ዶክተር ኤርጎጌ፣ በዚህም 38 ሚሊዮን ህዝብ በነጻ በማገልገል ከ7 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ማስቀረት መቻሉን አስታውቀዋል፡፡

በተባበሩት መንግሥታት የምስራቅና የደቡብ አፍሪካ አገራት ቀጠና የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ተጠሪ የሆኑት ሉሲ ዱንጉ በመድረኩ እንደተናገሩት፣ ባደረጉት ጥናት በአፍሪካ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት አፈጻጸም ከተለያዩ የዓለም አገራት ጋር ሲነጻጸር የተሻለ ደረጃ ላይ የሆነበት ምክንያት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሥራ በአፍሪካ ከጥንት ጀምሮ የሚከናወን ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡ በ2022 አፈጻጸምም ሪፖርት እንኳ አፍሪካ ሌሎችን አገራትን 17 ነጥብ 5 በመቶ ትበልጣለች፡፡

በበጎ ፍቃድ አገልግሎት በመንግሥትና በተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል ድልድይ በመሆን በቀላሉ ለመድረስ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ያስችላል ያሉት ሉሲ ዱንጉ፣ በተለይ በአፍሪካ ህዝቦች መካከል እኩልነት፣ አካታችነትና ፍትሀዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በጎ ፍቃድ አገልግሎት አይነተኛ መፍትሄ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ፋሲካ ሞላ እንደገለጹት፣ በአጼ ምኒልክ ጊዜ አገሪቱ በገጠማት ክፉ ቀን ተብሎ የሚታወቅ አስከፊ ረሃብ ለመግታት በርካታ በጎ ፍቃደኛ ወጣቶች ተሰማርተዋል፡፡ዛሬም ህዝቡ እንደ ትናንቱ በደቦ፣ በወንፈልና በሌሎች ዘዴዎች እየተደጋገፈ ይገኛል፡፡ በተለይ ከለውጡ ወዲህ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለበጎ ፍቃድ አገልግሎት በሰጡት ትኩረት በርካታ ደሳሳ ቤቶች ማደስ፣ ችግኞች መትከል፣ ድሆችን ማብላትና በሌሎች ዘርፎች የተመዘገቡ ውጤቶች አመርቂ ናቸው ብለዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ነፃ አውጪነት የህዝብን እውነተኛ ፍላጎት ማወቅ እና ለዚህም ተገዥ መሆንን ይጠይቃል

በአገራችን ከ1960ዎቹ ጀምሮ ፋሽን እየሆነ የመጣው "ነፃ አውጪ" የሚለው ቃል እስከዛሬ ድረስ ከፍ ያለ ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል። ነፃ ወጪውና አውጪው በአግባቡ ባልተለየበት፤ ከማንና ከምን ነፃ እንደሚወጣ የጠራ እውቀት ባልተያዘበት የአስተሳሰብ መሰረት ላይ የተጀመረው ይህ ንቅናቄ በቀደሙ ችግሮቻችን ላይ ተጨማሪ ችግር ከመፍጠር ባለፈ ያስገኘልን ትሩፋት እንደሌለም ይታመናል።

አጠቃላይ በሆነው አገራዊ ማህበረሰባዊ የአስተሳሰብ መሰረት ላይ ያልተዋቀረው የነፃ አውጪነት እንቅስቃሴዎች፤ ከሁሉም በላይ እራሳቸው በብዙ የስነ ልቦና ቀውስ ውስጥ ባሉ ግለሰቦችና የግለሰብ ስብስቦች /ቡድኖች / የመመራታቸው እውነታ ሁኔታዎችን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ በመሆን ከፍ ያለ ዋጋ እንድንከፍል አድርገውናል።

እነዚህ ቡድኖች ባለፉት 50 አመታት እንደ አገር ነጻ እናወጣዋለን ያሉትን መላውን ህዝብም ሆነ እንወክላችኋለን ያሏቸውን ብሔር ብሔረሰቦች ለአዲስና ለከፋ ባርነት ከመዳረግ ባለፈ የሚጨበጥ ነፃነት ባለቤት ሊያደርጓቸው አልቻሉም። ይልቁንም አንዳንዶቹ የነጻነት ትግሉን የቡድን ፍላጎት የጦርነት አውድማ አድርገውት ከስመው ሲቀሩ ሌሎች ደግሞ የአሸናፊነት መንፈስ በፈጠረው እብሪት ለውድቀት ተዳርገዋል።

ለሁለቱም ውድቀት እና የአሸናፊነት እብሪት በነጻነት ንቅናቄ ስም ውድ ሕይወቱን የገበረውና እየገበረ ያለው ተራው ሕዝብ የመሆኑ እውነታ፤ ከነጻነት ትግልና እንቅስቃሴ በስተጀርባ ያለውን ፌዝ ትክክለኛ እውነታ በግልጽ የሚያሳይ ነው። ከዛም በላይ ነጻነት የሚባለውም ሆነ በነጻነት ስም የሚካሄዱ ንቅናቄዎች የቱን ያህል ለተራው ህዝብ የከፋ መከራና ስቃይ ምንጭ መሆናቸውን የሚያመላክት ነው።

ይህ ደግሞ ባለፉት 50 አመታት ኢትዮጵያውያን እንደ ህዝብ በነጻነትና በነፃ አውጪዎች ስም የከፈሉትና ዛሬም በከፋ መልኩ አገረ መንግስቱን ስጋት ውስጥ በሚከት መልኩ እየከፈሉት ያለው ዋጋ ተጨባጭ ማሳያ ነው። ህዝባችን በየወቅቱ ተስፋዎቹን / ትውልዶችን ትርጉም አልባ ለሆኑ የነጻነት ትግሎች ገብሮ ለቁዘማ ሕይወት የተዳረገባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው።

ይህም ሆኖ ግን በነፃነት ስም በከፈለው መስዋዕትነት ለተሻለ ነጻነት ሳይሆን ለከፋ ባርነት የመዳረጉ እውነታ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ነፃ እወጣባቸዋለሁ ብሎ ዋጋ በከፈለባቸው የነፃነት ትግሎች ያሰበውንና የተመኘውን ማግኘት አልቻለም። ከዚህ ይልቅ የስነ ልቦና ቀውስ ውስጥ ባሉ ግለሰቦችና የግለሰብ ስብስቦች /ቡድኖች / ፍላጎት ማሟያ ሆኗል።

ለዚህ ደግሞ መላው ህዝባችን በብዙ ተስፋ የጠበቀውና ብዙ ዋጋ የከፈለለትን የ1966 አብዮት ጅማሬና ፍጻሜ፣ በ1983 የነበረውን የነፃነት ዲስኩርና ከዲስኩሩ በስተጀርባ የነበረውን ጠንካራ የብረት ሰንሰለት ማስታወስ ተገቢ ነው። ከሁሉም በላይ ስለ ነፃነት ከፍ ባለ ድምጽ ሲያዜምና ለዚህም ከፍ ያለ ዋጋ የከፈለውን የትግራይ ህዝብ ዛሬ ያለበትን ተጨባጭ እውነታ ማየት ተገቢ ነው። ይህ ህዝብ በተዜመለት የማይጨበጥ የነፃነት ዜማ ስቶ በብዙ መስዋዕትነት በእጁ ላይ የከፋ የባርነት ሰንሰለት ካጠለቀ 40 አስርቶች አልፈውታል።

ሕዝቡ በነፃ አውጪነት ስም የተሰባሰቡ ግለሰቦች /የአሸባሪው ሕወሓት የግል እቃ እስኪመስል ድረስ ለቡድኑ የፖለቲካ ህልውና መደራደሪያ እስከመሆን ደርሷል። እንደ ህዝብ የራሱ ፈቃድ እንደሌለው፤ በነፃነት ስም የፖለቲካ ቁማር መቆመሪያ ካርድ ሆኗል። ይህ ደግሞ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ነፃ አውጪነት ከሁሉም በላይ በአመጸኝነት መንፈስ ጠላት ፈጥሮ መሳሪያ ታጥቆ በረሀ /ጫካ/ ከመግባት ያለፈ ያለተዛነፈ የስነ ልቦና ውቅር የሚፈልግ ነው። ነፃ አወጣዋለሁ የምትለውን ህዝብ መንፈሳዊ፣ ባህላዊ እና ማህበራዊ እሴቶችን በአግባቡ ማወቅን፣ ከዚህ የሚመነጨውን ማህበራዊ ስነልቦናውን መረዳትን የሚጠይቅ ነው።

ከዚህም በላይ ስለ ነፃነትም ሆነ ስለ ነፃ አውጪነት ከማሰብ በፊት ቀድሞ ከየትኛውም አይነት የተዛነፈ የስነ ልቦና ቀውስ ነፃ መውጣትን ይጠይቃል። የህዝብ እውነተኛ ፍላጎትን ማወቅ እና ለዚህም ተገዥ መሆንን ይፈልጋል። ህዝብን የፖለቲካ ቁማር መቆመሪያ ካርድ አድርጎ መሳብን አብዝቶ መጠየፍ ይሻል።

ህዝብን ያለ አንዳች ሰብዓዊ ርህራሄ ትርጉም ለሌለው ጦርነት እየማገዱ፤ የህዝብን ተስፋ ወደ ቁም ቅዠት እየለወጡ ፍጹም በሆነ ድፍረት ነፃ አውጪ ነኝ ብሎ መጮህ የእብደት ሁሉ እብደት፤ ፍፁም የሆነ የአመጽ ልጅነት መገለጫ ነው!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# በሂደት የሚመለሱ...

ዶክተር ጀኔኑስ

‹‹ካያያዝ ይቀደዳል ካነጋገር ይፈረዳል›› ይላል የአገሬ ሰው። አንዳንድ ጊዜ እንዳመጣልን የምንናገረው፤ እንዳሻን የምንመነዝረው ነገር ከጊዜ በኋላ ሊያመጣ የሚችለውን ውጤት መገመት ይሳነናል።

ትዝ ይለኛል፤ የአሸባሪው ሕወሓት የስልጣን ዘመን እንዳበቃ በርካቶች በመገናኛ ብዙሃን እየወጡ ቡድኑን እየኮነኑ ራሳቸውን እንደፃድቅ መቁጥር ጀምረው ነበር። በሂደት ደግሞ የለውጥ ሃዋርያ ነን ሲሉም ተሰምተዋል፤ እኛም እስቲ ይሁን አልን። ታዲያ እነዚህ አካላት ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለውጡ እኛ እንደፈለግነው አልሄደም ብለው በጥቂት ወራት ውስጥ ማኩረፍ ጀመሩ። እንደ ጨቅላ ህፃን አባብሉን፤ ዳይፐር በየደቂቃው ቀይሩልን ማለቱን ተያያዙት። ሕወሓት ጨቋኝ ነው ሲሉ ቆይተው ከእሱ በላይ ጨቋኝና አረመኔ መሆን ፈለጉ።

ነፃ እናወጣለን ብለው ጭራሽ ነፃነት ቃሉ ጠፋቸው። በየመንደሩ መተናኮልና ከመንግስት ጋር እሰጣ ገባ ጀመሩ። ትጥቅ ፍቱ ሲባሉ ‹‹ፈቺ ማነው አስፈቺውስ?›› ብለው ደረታቸውን ነፍተው የፀጥታ ችግር ሆኑ። ውል አልባ ፖለቲካቸውን መሰብሰብ አቅቷቸው ህዝብን ለከፋ ችግር መዳረግ ጀመሩ። ለዚህም ለአብነት ያህል ሸኔን፣ የቤንሻንጉል ነፃ አውጪ ግንባርን፣ የቅማንት ኮሚቴ የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

የጠራ ፖለቲካ ፍልስፍና እና አካሄድ ሳይኖራቸው አሸባሪውን ሕወሓት እየጠሉ ራሳቸው በሚፈጥሩት ሴራ እና ተንኮል ከሕወሓት በላይ የሚጠሉና አስነዋሪ ሆነው አረፉ። አገር ጭንቅ ላይ በሆነችበት ሰዓት መንግስትን ለመጣል ከሥር መገዝገዝ ከኋላ መውጋት ጀመሩ። ጭራሽ ሸኔ ከሕወሓት ጋር በመሆን ማዕከላዊ መንግስትን እየወጋ ስለመሆኑ የጃል መሮ የስልክ መረጃ ልውውጥ ይፋ ሆነ። ሌሎችም ጫካው ጥራኝ ብለው ለውጥ አመጣልን ያሉትን መንግስት ላይ ቃታ መሳብ ጀመሩ።

ቆመ ጠብቀኝ የጦር መሳሪያ እና ቆመህ ጠብቀኝ በሆነ የፖለቲካ አካሄድ በብዙ መንገድ የተጠናከረውን መንግስት እንገረስሳለን አሉ። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ነገር ቢኖር ፍላጎታቸው ከባድ ነው። እነዚህ አካላት ለቀቅ ቢደረጉ እንኳን ህዝብን ከህዝብ እያጫረሱ ኢትዮጵያን በመበታተን ለግብፅ እና የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ተላላኪነታቸውን የሚመሰክሩ እንጂ ምንም የሚፈይዱ አይሆኑም።

ታዲያ የኢትዮጵያ ህዝብ እውነታውን በመረዳት በአሁኑ ወቅት አንቅሮ እየተፋቸው ነው። በተገኙበት እርምጃ እየወሰደባቸውም ይገኛል። ይህ የሚያሳየው ይህ ቆሞ ቀር የሆነ የፖለቲካ እሳቤያቸው የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በዚህ አገር ላይ ዋጋ አልባ ስለመሆኑ ነው።

ይሁንና እነዚህን ፀረ-ሰላም ሃይሎችን እንቅስቃሴ ለመግታትና ሁኔታዎችን ለማስተካከል በሚደረገው ጥረት ብዙ ፈተናዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ማሰብ ባይከብድም አሮጌ አስተሳሰባቸው ተቀብሮ አዲስ የፖለቲካ እሳቤ በኢትዮጵያ ሰማይ ስር መድመቁ አይቀሬ ነው።

በእርግጥ አዲስ የፖለቲካ እሳቤን አገራዊ መሰረት ማስያዝ በአንዲት ጀንበር የሚሆን አይደለም። ሂደት ይፈልጋል፤ የህዝብን ተሳትፎ ይፈልጋል፤ መስዋዕትነት ይፈልጋል። ለዚህ ደግሞ እራስን በተገቢው መንገድ ማዘጋጀት ወሳኝ ነው።

አሁነኛው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነው። እንደቀደሙት ዘመናት የሽግግር ወቅቶች በኪሳራ እንዳይጠናቀቅ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። በብዙ ጥቅም የተሳሰሩ የፖለቲካ ሐይሎች በአገራዊ ፖለቲካ መድረኩ ላይ አሉ አንዱ ሲነካ ሌላው ኡኡታውን ያስነካዋል። ከአገር ውስጥ እስከ ውጭ ድረስ በጥቅም የተሳሰሩ አካላት ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪ መስለው ይጮኻሉ።

በአንድ ወቅት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በፓርላማ መደበኛ ስብሰባ ላይ በጣም ያረጁ ተሽከርካሪዎች ለምን ከመንገድ ላይ በፍጥነት ዘወር አይደረጉም የሚል ይዘት ያለው ጥያቄ እንደቀረበላቸው አስታውሳለሁ። ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚመጡ ጎብኚዎችን በየመንገዱ እየተገተሩ የሚያስተናግዱ 30 እና 40 ዓመታትን ያሳለፉ ላዳ መኪናዎችን ከመንገድ ይወገዱልን ለሚለው የህዝብ እንደራሴዎች ጥያቄ እንዲህ የሚል ምላሽ ሰጥተው ነበር።

‹‹ችግሩ አገባቡ ላይ አይደለም አወጣጡ ላይ ነው። በየዳገቱ እያረፈ የሚሄደውን መኪናም ቢሆን ከመንገድ ውጭ ማድረግ የሚያስችል አሠራር አለ። ነገር ግን አፈፃፀሙ አስቸጋሪ ይሆናል። ምክንያቱም በዚህች መኪና ላይ የተንጠለጠለ ህልውና ያለው ቤተሰብ አለ። እናም ይህችን መኪና ከሥራ ውጭ ስናደርግ አማራጭ የሥራ ዕድል እየፈጠርን ነው ወይ የሚለውን ማየት ይኖርብናል።

ከቅደም ተከተሉ ጋር እያያዝን ነው እንጂ ዋናው ጉዳይ ከጥቅም ውጭ መሆን የሚገባቸው መኪኖች አለመኖራቸው አይደለም። ሌላው ቀርቶ የቤተመንግስት መኪኖችም በንጉሱ ዘመነ መንግስት ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ተብለው የተገዙ መርቸዲስ መኪኖች ናቸው እስካሁን ድረስ ጥቅም ላይ የሚውሉት። አንዳንድ ጊዜም እንግዳ እንደያዙ ዳገት ላይ ያርፋሉ። በጣም ለብዙ ዓመታት በማገልገላቸው በቱሪስት መስህብነት ደረጃ የሚመረጡ መኪኖች ናቸው። ከአገልግሎት አንፃር ግን ችግር አለባቸው። በመሆኑም እነሱን ለመተካት ሙከራ እየተደረገ ይገኛል። ነገር ግን የሌላውን ህብረተሰብ መኪና መተካት የመንግስትን መኪና የመተካት ያክል ቀላል አይደለም» ብለዋል

ውድ አንባቢያን፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሰጡት ምላሻ አሮጌ መኪኖችን ስለመቀየር ለተጠየቁት ጥያቄ ነው፤ እኛ ግን አሁን እየተነጋገርን ያለነው አሮጊ የፖለቲካ አስተሳሰብን ስለመቀየር ነው። ይህ ነገሮች የቱን ያህል ውስብስብ እንደሆኑ ለማሳየት እድል የሚሰጥ ይመስለኛል። ነገሮችን በቀላሉ ማድረግና መከወን ቢቻል መንግስትም እስካሁን ባልዘገየ ነበር የሚል እምነት አለኝ።

አንዲት ተሽከርካሪ በተነካች ቁጥር የበርካቶችን ሕይወት እንደሚዳስስ ሁሉ በሽግግር ወቅት በተለይም አገር በአሁን ወቅት ባለችበት አስቸጋሪ ወቅት አንድ በወንጀል የተጠረጠረ ግለሰብ ሲታሰርም የታሳሪውን መታሰረ የፖለቲካ መቆመሪያ ለማድረግ የሚጮሁ ድምጾችን ብዛትና የጩኸቱን ከፍታ መገመት አያዳግትም።

መንግስት ይህን እውነታ ታሳቢ በማድረግ አንዳንዶችን በሆደ ሰፊነት ለማለፍ እየተገደደ ይመስለኛል። አንዳንዶቹን ደግሞ በሂደት ከጥፋታቸው ይማራሉ አሊያም ሕይወት ያስተምራቸዋል ከሚል እሳቤ በዝምታ ሊያልፋቸው እንደወሰነ ይሰማኛል።

በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ እንደተናገሩት፤ በመታሰር መጀገን የሚፈልጉ በርካታ አካላት እና ግለሰቦች እንዳሉ መታዘብ ጀምረናል። በወንጀል ተጠርጥረው የነበሩ አካላት በዋስ ከተለቀቁበት ወንጀል እንኳን ነፃ ሳይባሉ በወራት ልዩነት ደግመው ወደለመዱት ቤታቸው ወይንም ማረሚያ ቤት ሲመለሱ እያየን ነው።

ይህ የሚያሳየው ጥፋትን ሆን ብሎ በመደጋገም መንግስትን እየተፈታተኑ በእስር የመጀገን የተዛነፈ የስነ ልቦና ቀውስ እየተፈጠረ መሆኑን አመላካች ነው። እንደዚህም ሆኖ ግን መንግስት ብዙ ነገሮችን በዝምታ እያለፈ ነው። በዚህ ውስጥ በግልጽ መረዳት የሚቻለው መንግስት በሂደት ይስተካከላሉ ብሎ የሚያምናቸው በርካታ ነገሮች እንዳሉ ነው።

ኢትዮጵያን ለመታደግ ሲባል ብዙ መሰዋዕትነት እየተከፈለ ባለበት ታሪካዊ ወቅት ይህ ትዕግስት ለጊዜው መንግስትን ቸልተኛ ያስብለው፤ ያስተቸው ይሆናል እንጂ ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ማበብ ግን የራሱ የሆነ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል ብዬ አምናለሁ። ከዚህም በተጨማሪ ነገሮች በሂደት እንደሚስተካከሉና ጊዜ የማይመልሰው ነገር አለመኖሩን ከመረዳት የሚመነጭ አስተዋይነት እንደሆነም እረዳለሁ።

# ስራሳችን ስንል ሰው መሆን አለብን

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ሰውነት የአምላክ መልክና አምሳል ነው። በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰውን ለመፍጠር ሲነሳ ራሱን ነው የተጠቀመው። የራሱን መልክና አምሳል አርዐያም ነው የወሰደው። ‹ሰውን በአርያና በአምሳላችን እንፍጠር› ሲል። ሰው የፈጣሪ ቤተ መቅደስ ነው። በሀጢዐት ሊረክስ፣ በበደል ሊቆሽሽ አልተፈጠረም። ከዚህ እውነት በመነሳት የሰውነትን ባህሪያት መረዳት እንችላለን ብዬ አስባለው። ሰው ራሱን በሀጢዐት፣ በበደል፣ በነውር ዝቅ እስካላደረገ፤ ሰው ራሱን በክፋት፣ በጭካኔ፣ በመጥፎ ግብር እስካላረከሰ ድረስ አፈጣጠሩ አስደናቂ ነው። ማንነታችን ይሄ ሆኖ ሳለ እኛ ግን ከዚህ ድንቅ ተፈጥሮአችን በተቃራኒ የቆምን ነን። ዘፍጥረት ላይ እግዚአብሄር አምላክ ሰውን በመፍጠሩ የተጸጸተበት ታሪክ አለ።

ይሄ ብቻ አይደለም ሰው ልቡ ክፉና የማይመረመር እንደሆነ ይሄው ምዕራፍ ይናገራል። ይሄን ሁሉ ትተን ኖህና ቤተሰቡ ብቻ የዳኑበትን የጥፋት ዘመን ብናይ በሰው ልጅ ክፋት የመጣ እንደሆነ እንደርስበታለን። ሌላም ሳይንሳዊ እውነት ..አለም ላይ ካሉ አስር እጅግ አደገኛ እንስሳት ውስጥ ቁጥር አንድ ደረጃን የያዘው ሰው ነው። እንግዲህ አስቡት ለክብርና ለሞገስ ተፈጥሮ ሰው አለም ላይ ካሉ እንስሳት ሁሉ በክፋቱ ቀዳሚ ሲሆን። አስቡት ከየትኛውም ፍጥረት ተለይቶ በፈጣሪ አምሳል ተፈጥሮ አውሬነትን ተላብሶ ሲኖር። የሚያስብበት አእምሮ፣ የሚረዳበት ልቦና ተሰጥቶት የሀጢዐት አለቃ ሲሆን።

የአፈጣጠራችን ታሪክ የሚነግረን በጎ አስበን፣ በጎ አድርገን በጎውን እግዚአብሄርን እንድንመስል ነው። ጽድቅ ሰርተን፣ ጽድቅ አውርተን የክብር መንግስት እንድንወርስ ነው። ሰው የሆነው ለሰው ልጅ ሁሉ አስፈላጊዎች እንድንሆን ነው። ሰው የሆነው እንድንራራና እንድናዝን ነው። በእጃችን ሰይፍ እንድንጨብጥ አልተፈጠርን። በእጃችን ደም እንድናፈስ፣ በእጃችን ንጹሀንን እንድንበድል ሰው አልሆንም። በስልጣናችን ሌሎችን እንድናስጨንቅ አልተፈቀደልንም። እንድንበቀልና እንድንፈርድ አልተፈጠርንም። በቀልና ፍርድ የአምላክ ነው።

በታላቁ መጽሀፍ ኤፌሶን 2 ከቁጥር 10 ላይ ስለ ሰውነት የተነገረ አንድ ጥቅስ አለ እንዲህ ይላል ‹መልካሙን ስራ እንድንሰራ በክርስቶስ እየሱስ ተፈጠርን› ይላል። በቃ ሰውነት ይሄ ነው። እኛ ሰው የሆነው በበጎ ሀሳብ በጎ ነገር ለመስራት ብቻ ነው። ስለዚህም ራሳችንን መረዳት ይኖርብናል። ለምን ሰው እንደሆንን፣ ፈጣሪ ለምን እኛን በአርዐያና በአምሳሉ አልቆ እንደፈጠረን መመርመር ይኖርብናል። ታላቁ ፈላስፋ ሶቅራጥስ ‹ያልተመረመረ ህይወት ዋጋ የለውም› ይላል እውነት ነው ያልተመረመረ ህይወት ዋጋ የለውም። ራሳችንን መመርመር አለብን። ሀሳባችንን ተግባራችንን መፈተሽ ይኖርብናል።

> እኛ ሰው የሆነው በበጎ ሀሳብ በጎ ነገር ለመስራት ብቻ ነው። ስለዚህም ራሳችንን መረዳት ይኖርብናል። ለምን ሰው እንደሆንን፣ ፈጣሪ ለምን እኛን በአርዐያና በአምሳሉ አልቆ እንደፈጠረን መመርመር ይኖርብናል። ታላቁ ፈላስፋ ሶቅራጥስ ‹ያልተመረመረ ህይወት ዋጋ የለውም› ይላል እውነት ነው ያልተመረመረ ህይወት ዋጋ የለውም

አሁን ላይ በሰውነታችን እያደረግናቸው ያሉ ነገሮች እኛንም ሆነ ሌሎችን የሚጎዱ ናቸው። አገራችን ላይ የተፈጠሩ አብዛኞቹ መጥፎ ታሪኮች በሰው ልጅ መጥፎ ሀሳብ የተፈጠሩ ናቸው። አሁንም እንኳን ሀሳቦቻችንን መግታት አቅቶን ችግር እየፈጠርን ነው። ሰው ሰውነቱን ሲረዳ በብሄር አይባላም። የኔነት ስሜት አይገዛውም። በዘርና በቀለም አይገፋፋም። ምክንያቱም ይሄ አለም የእኛ አይደለምና። ሰው ሰውነቱን ሲረዳ ሌሎችን ማፍቀር ነው የሚጀምረው። ሰው ሰውነቱን ሲረዳ ጥልና መገፋፋት ሰይጣናዊ እንደሆኑ ነው የሚረዳው። ሰው ሰውነቱን ሲረዳ ተነጋግሮ መግባባትን ነው የሚያስቀድመው። ምክንያቱም ከአምላክ የተማረው ይሄ ነውና። ሰው ሰውነቱን ሲረዳ ለበቀል ድንጋይ አያነሳም፣ ሰይፍ አይመዝም። ሰው ሰውነቱን ሲረዳ ለመገፋፋት አይፈጥንም፣ ለሀጢዐት አይቸኩልም ምክንያቱም የዐጢዐት ደሞዝ ሞት ነውና። ሰው ሰውነቱን ሲረዳ የኔ የሚለው አንዳች ያጣል፣ በብሄርና በጎሳ አይባላም። በቦታና በአካባቢ አይጣላም ምክንያቱም አገሩ በሰማይ እንደሆነ ነው የሚረዳው። መጽሀፍ ቅዱስም አገራችን በሰማይ ነው ይላልና።

ክቡር ዶክተር ከበደ ሚካኤል ሁሉም በሚረዳው ቀላል ቋንቋ ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል የሚነኩ በሀሳብ የገዘፉ ግጥሞችን በመጻፍ ይታወቃሉ። ሰውነቱ የጠፋበትን መደዴ ገላ ሸንቆጥ ለማድረግ እንዲሁም ደግሞ ከኩነኔ ጽድቅ፣ ከክፋት ደግነት እጅጉን የሚልቁበትን መንገድ ለማሳየት ‹ጽድቅና ኩነኔ ቢኖሩም ባይኖም፣ ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም› ሲሉ ገጥመዋል። እውነት ነው ከክፋት ደግነት እጅጉን ይልቃል። ደግነት የመልካም ነፍሶች ህብስት ነው። በፍርድ ቀን ፈጣሪ የሰውን ልጅ የሚጠይቀው ጥያቄ ‹ምድር ላይ በሰጠሁህ እድሜ ምን በጎ ነገር ሰራህ ብሎ ነው። ፈጣሪ ፊት ስንቆም የሚሟገቱልን በጎ ስራዎቻችን ናቸው። ግንባራችን ላይ ተጽፈው ለፍርድ የሚያበቁን አሁን ላይ እያደረግናቸው ያሉ የጽድቅ ስራዎች ናቸው።

በሰጠኋችሁ እድሜ፣ በሰጠኋችሁ ሰውነት፣ በሰጠኋችሁ ህሊና ምን አደረጋችሁበት ተብለን ስንጠየቅ ሞገስ የሚሆኑን ዛሬ እያደረግናቸው ያሉ በጎ ስራዎች ናቸው። በሰጠኋችሁ እውቀት፣ በሰጠኋችሁ ስልጣን ምን አደረጋችሁበት ተብለን ስንጠየቅ መልስ የሚሆኑን ስራዎቻችን ናቸው። በፍርድ ቀን የምንዋረደውም ሆነ የምንከብረው በሀሳባችን በጉል በሚወጣው ድርጊት ነው። ዛሬ የነገ ቅርስ ነው። የሁላችንም ነገ የሚሰራው በዛሬ ሀሳብና ድርጊት ነው። ሰው በሀሳቡ መልካም ሲሆን በድርጊቱም መልካም ነው የሚሆነው። ድርጊት ህይወት ነው። በህይወታችን ላይ የሚንጸባረቁ እኩይም ይሁኑ በጎ ልማዶቻችን በሀሳብና በድርጊታችን የጸነስናቸው ናቸው።

ሰው በጎ ሲሆን ሰይጣንን ነው የሚያሳፍረው መጥፎ ሲሆን ደግሞ አምላኩን። አምላክ ያፍራል እኮ..የፈጠረን እኛ ህግና ትዕዛዙን ሽረን አውሬ ስንሆንበት ያፍራል። በዚያው ልክ ደግሞ ሰው ፈጣሪውን ማሳቅ ይችላል። አምላክ የሚስቀው በእኛ በጎነት ነው። በዙሪያችን ድሆችን ስንረዳ፣ መከረኞችን ስንታደግ እግዜር ይስቃል። ለበደሉን ይቅርታ ስናደርግ፣ ለጠሉን ትዕግስትን ስናበዛ ሰይጣን ያፍራል እግዜር ይከብራል። በእኛ ክፋት ክብር የሚያገኘው ሰይጣን ብቻ ነው። ሰው በሀሳቡና በድርጊቱ መጥፎ ሲሆን አጋንትን ነው የሚያስደስተው። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እየሰራነው ካለው ስህተት መለየት ይኖርብናል።

በዙሪያችን የእኛን በጎ መሆን የሚሹ በርካታ ነፍሶች አሉ። በዙሪያችን የእኛን እጅ፣ የእኛን እውቀት፣ የእኛን ራሮት የሚሹ እልፍ ሰውነቶች አሉ። አገራችን ያለችበት ሁኔታ ይታወቃል። ብዙ የተፈናቀሉ፣ ብዙ የተጎዱ፣ ብዙ የተራቡ ዜጎች አሉን። ብዙ የታረዙ፣ ብዙ ያዘኑ፣ ብዙ የታመሙ ዜጎች አሉን ለነሱ እንድረስላቸው። መማር እየፈለጉ ግን ደግሞ በአቅራቢያቸው ትምህርት ቤት ያጡ አሉ ለነሱ ትምህርት ቤት እንገንባላቸው። ንጹህ ውሀ የሌላቸው፣ ጤና ጣቢያና የህክምና ቁሳቁሶች ያጡ ሆስፒታሎች አሉ እነሱን እንያቸው። ደግ መሆን ከቻልን ደግ ልንሆንባቸው የሚችሉ በርካታ አጋጣሚዎች አሉ። ድሀ አገርና ድሀ ህዝብ መሀል እየኖርን የእኛ በጎ መሆን ማለት ዋጋው በምንም የማይተመን ነው።

አሁን ላይ በረከቶቻችንን እያራቅን ያለነው ራሳችን ነን። እንደ ዜጋ ጥሩ ብናስብና ጥሩ ብንሰራ ድህነታችን በዚህ ልክ ዘልቆ ባልተሰማን ነበር። እንደ መንግስት፣ እንደ ተፎካካሪ ፓርቲ ጥሩ ብናስብና፣ ጥሩ ብንሰራ ከራሳችን አልፈን ለሌሎች የሚተርፍ የሰላምና የአንድነት ምኩራብ እንገነባ ነበር። አሁን ላይ ከሰውነት የወጣን ብዙዎች ነን። በሰውነት ጭንብል አውሬ ሆነን የምንኖር ሞልተናል። አገር ሰው ነው የሚያስፈልጋት። አገር አስታራቂ፣ ይቅር ባይ ነው የሚያስፈልጋት። አገር እግዚአብሄርን የሚፈራ ትውልድ ነው የሚያስፈልጋት።

አገር ነውር የሚያውቅ፣ የአባቶቹን ስርዐት የሚያከብር ዜጋ ነው የሚያስፈልጋት። በዚህ እውነት ውስጥ ራሳችንን እስካልገነባን ድረስ በተላበስነው የአውሬነት ባህሪያት የባሰ እንጂ የተሻለ ለውጥ አናመጣም። ለራሳችን ስንል ሰው መሆን አለብን። አገራችን አሁን ሰው ነው የሚያስፈልጋት። ሰው ስላችሁ ጭንብል ለባሹን ማለቴ አይደለም። የበግ ለምድ ለብሶ እንደ ተኩላ የሚንቀሳቀሰውን ማለቴ አይደለም። በሀሳቡ አገር የሚፈጥረውን፣ በተግባሩ ትውልድ የሚቀርጸውን እሱን ማለቴ ነው። እውቀትና በምክንያታዊነት የሚራመደውን ማለቴ ነው።

ብዙዎቻችን የሚጠቅመን እያለ የማይጠቅመንን የምናደርግ ነን። ዛሬ የምንሳራቸው ክፉ ነገሮች ሁሉ የነገ መንገዳችንን በእሾህ ከማጠር ባለፈ የሚጠቅሙን አይደሉም። ዛሬ ላይ በክፋት የዘራናቸው ቡቃያዎች ነገ ላይ ዛፍ ሆነው እኛ ላይ ነው የሚወድቁት። ዛሬ ላይ በጥላቻ ያሳደግናቸው ችግኞች ነገ ላይ የሞት ፍሬ ነው የሚያበቅሉት። ዛሬ ላይ ተንከባክበን የያዝናቸው የብሄርና የእኔነት ስሜቶች ነገ ላይ ይዘውን የሚጠፉ ናቸው። የመበላሸትም የመስተካከልም ነጻ ፍቃድ አለን። ታዲያ ሰው መሆን ለምን አቃተን? ራሳችንን መጠበቅ ካልቻልን አለም የውበቷን ያክል ሊያቆሹሹን የሚችሉ በርካታ ጉድፎች አሏት።

የገዛ ሰውነታችን በፈጠራቸው አለማዊ ሀጢዐቶች ተከበን የምንኖር ነን። አሁናችን ውስጥ ብዙ ነገር አለ። እየመረጥን መስማት፣ እየመረጥን ማየት፣ እየመረጥን ማሰብ የእኛ ፈንታ ነው። ከፍ ብዬ እንዳልኳችሁ ሰውን ያቆሸሸው ሀሳቡና ምግባሩ ናቸው። ምድርን ገሀነም ያደረጋት የሰው ልጅ የተዛባ አመለካከት ነው። አጢነን ካየነው ሁሉም ነገር በተፈጥሮው ውብና ማራኪ ነው። የሰው ልጅ ክፋት፣ የሰው ልጅ ራስ ወዳድነት ግን ይሄን የተፈጥሮ መልክ አወየበው። ሰው ለክብር ተፈጥሮ ለመከራ መኖሩ ይገርመኛል። ለከፍታ ተፈጥሮ ዝቅታን መምረጡ ያስደንቃል።

አለም በሰው ልጅ የተሰቃየችውን ያክል በምንም ተሰቃይታ አታውቅም። ተፈጥሮ በሰው ልጅ የተበላሸችውን ያክል በምንም ተበላሽታ አታውቅም። የሰው ልጅ በራሱ የሰው ልጅ የተጎሳቆለውን ያክል በምንም ተጎሳቁሎ አያውቅም። አብዛኛው የሰው ልጅ መከራ ራስ ወዳድነት የፈጠረው ነው። ከእግዚአብሄር መራቅ የፈጠረው ነው። በአገራችን እየሆነ ያለውም ይሄን እውነት የሚያስረግጥ ነው። አገራችን በራስ ወዳዶች ስትሰቃይ ኖራለች አሁንም እየተሰቃየች ነው። ህዝባችን በራስ ወዳዶች ሀሳብና ምኞት ሲጎሳቆል ነበር አሁንም እየተጎሳቆለ ነው።

አልታወቀንም እንጂ ማንም ሳይደርስብን፣ ማንም ሳይነካን ራሳችንን በራሳችን እየጎዳን ነው። አልገባንም እንጂ ራሳችን ለራሳችን መከራ ሆነን እየኖርን ነው። አልተረዳንም እንጂ የራሳችን ጠላቶች ራሳችን ነን። ከማንም ባልሆነ ከእኛው በሆነ ሀሳብና ድርጊት እየተሰቃየን ነው ያለነው። ሰው የራሱ ጠላት ሲሆን አደገኛ ነው። ሰው የራሱ ጠላት ሲሆን በራሱ ላይ የእሳት ፍም ነው የሚቆልለው። እኛም አሁን የራሳችን ጠላቶች ነን። በዘመነ ሀሳብ፣ በእግዚአብሄራዊ ሰውነት ነውሮቻችንን እስካላጸዳን ድረስ ሁሌም የብሄር፣ ሁሌም የእኔነት በሽተኞች ነው የምንሆነው። ሁሉም የጥላቻ፣ ሁሌም የመገፋፋት ህመምተኞች ነው የሚወጣን። ሁሌም የሀጢዐት፣ ሁሌም የማነስ መንፈስ ነው የሚጎበኘን። ሰው እንሁን..በፈጠርናቸው ችግሮች አንነስ። የፈጠርናቸው ነውሮች አያጥፉን።

ሰው ነን አይደል? በፈጣሪ አርዐያና አምሳል ተፈጥረናል አይደል? እናንተ የእግዚአብሄር ቤተ መቅደሶች ናችሁ ተብለናል አይደል? የሚያስብ አእምሮ ተሰጥቶናል አይደል? እኔን ምሰሉ ሲል ህያው ቃሉ ነግሮናል አይደል? የሀጢዐት ደሞዙ ሞት እንደሆነ እናውቃለን አይደል? በጎነት የህይወት አክሊል እንደሆነ ይሄንንም እናውቃለን አይደል? ታዲያ ሰው መሆን ለምን አቃተን? ‹ቀኑን ሙሉ እግዚአብሄርን በመፍራት እንኑር› ምሳ 23፥17

# አገር በቀል ማህበረ-ባህላዊ እሴቶችን ወደ ዘመናዊ ተቋምነት

## (“ቡሳ ጎኖፋ” እንደ ማሳያ)

ገርማ መንግሥቴ

"አገርኛ" ምንጫቸው፣ መነሻቸው፣ መገኛቸውም ሆነ ሙሉ አድራሻቸው አገር ውስጥ የሆኑ፤ ባለቤታቸውም ሆነ ፈጣሪ ተጠቃሚያቸው ኢትዮጵያዊ(ያን) የሆኑ ተቋማትም ሆኑ ሌሎች አገር በቀል ሀብቶች ናቸውና ሲያስተናግድ ቆይቷል።

አገር በቀል የሆኑ ድርጅቶች፣ ባህላዊ አልባሳት፣ ኢትዮጵያዊ የሆኑ በጎ አድራጊ ግለሰቦች፣ ለኢትዮጵያ ችግር ኢትዮጵያዊ መፍትሄ አፈላላጊ አካላት፣ ቡድኖች፣ ተቋማት ወዘተ ሁሉ አገራዊ ናቸውና አምዱ በሚገባ ሲያስተናግዳቸው ቆይቷል። "ቡሳ ጎኖፋ"ም የዛሬው ትኩረታችን ነው። ከሁሉም በፊት ለአጠቃላይ ግንዛቤ ያግዘን ዘንድ "አገር በቀል እውቀት"ን እንመልከት።

ሰሞኑን የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር "አገር በቀል እውቀቶች - በእጅ [እንደ] ያዙት ወርቅ ... ይቆጠራል!" በሚል ርእስ የተለያዩ ጥናቶችን ጠቅሶ ለንባብ ባበቃው ጽሑፍ "አገር በቀል እውቀት ማለት በውስን አካባቢዎች ላይ በኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ገጽታዎች ዙሪያ ላሉ ክፍተቶች መፍትሄ ይሆኑ ዘንድ ባህላዊ በሆነ መንገድ በአንድ ወይም በተወሰኑ ሰዎች የሚመነጭና የሚተገበር እውቀት ነው።" በማለት አስፍሯል። "የማህበረሰብ እውቀት"ን ደግሞ "ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ የሕይወት ገፅታዎች የሚዳሰሱበትና መፍትሄ የሚሰጥበት የተገለፀና ያልተገለፀ እውቀትና ልምድን ያጠቃለለ ነው።" ሲል ይበይነዋል። እነዚህን በአግባቡ አልምቶ ከመጠቀም አኳያ ያለንበትንም ሁኔታም "ነገር ግን በአገሪቱ የሚስተዋሉ ፈርጀ ብዙ ችግሮቻችን አገር በቀል እውቀቶችን ተጠቅሞ መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ፤ ከሌሎች አገሮች (ከምዕራባውያን) ተሞክሮ ተቀድ[ተው] የሚወሰዱ እርምጃዎች ችግሮቻችንን 'በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" አድርገውታል። ይህም አሁን አገሪቱ ለገባችበት ምስቅልቅል አንዱ ምክንያት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።" ሲል ከማሳሰቢያ ጋር ከገለፀ በኋላ "ሆኖም እንደ ገዳ፣ አባጋር ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ ለአገር ዕድገት እና ለሰላም ግንባታ መሠረት የሆኑ አገር በቀል እውቀቶች ባለቤት ብንሆንም፤ "በእጅ የያዙት ወርቅ ... ይቆጠራል" እንዲሉ አበው እነዚህን እውቀቶች በቅጡ እንዳላለማናቸውና እንዳልተጠቀምንባቸው" ይገልፃል። ተጠቅመን ቢሆን ኖሮ የት እንደምንደርስና ወደ ፊት አልምተን ልንጠቀም እንደሚገባም በዝርዝር ያስረዳል። ይህ ቀጥለን ለምንቃኘው "ቡሳ ጎኖፋ" ተቋም መሰረት ይሆነን ዘንድ ይዘነው ወደ ተነሳንበት እንዝለቅ።

የዛሬው "አገርኛ" የሚቃኘው አገር በቀል እውቀት የሆነውን፣ "ቡሳ ጎኖፋ" ማህበረ-ባህላዊ እሴትን ሲሆን፤ ይህ እሴት አስፈላጊውን ሁሉ አሟልቶ በመገኘቱ እራሱን ችሎ፤ እራሱንም ሆኖ፤ ቀድሞ የነበረውን የክልሉን አደጋ ስጋት ቢሮ ወደ ራሱ አምጥቶና በስሩ አድርጎ ወደ ዘመናዊ ተቋምነት ስለመሸጋገሩ ጉዳይ ነው።

ጨፌ ኦሮሚያ እያካሄደ በነበረው 1ኛ ዓመት 6ኛ የሥራ ዘመን 2ኛ መደበኛ ጉባኤ የገዳ ስርአት አካል በሆነው ስርአት "ቡሳ ጎኖፋ" የተሰኘ አዲስ አዋጅ መጽደቁ ከተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ተሰማ። የመረጃው ምንጭም ስለ አዋጁ ያስረዱት የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ሽመልስ አብዲሳ መሆናቸው፤ ስለ አዋጁ አስፈላጊነትም የኦሮሞን ሕዝብ አቃፊነቱንና የመረዳዳት ባህሉን ማንሳታቸው፤ አዋጁ ቀደም ሲል በገዳ ሥርዓት ውስጥ ያለና የቆየ ሥርዓት ሲሆን፤ (በተለይም በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ በተስተዋለው ድርቅ እና ጦርነት ወቅት ያሳየውን መደጋገፍ በምሳሌነት በማንሳት) የሕዝቦች የመረዳዳት እና መደጋገፍ ባህልን የሚያሳድግ፤ እንዲሁም፣ የመስጠት ባህልን የሚያጎለብት መሆኑን መግለፃቸው ከእነዚሁ ምንጮች ታወቀ። "ገዳ የሰው ልጅ መተዳደሪያ እንጂ የፖለቲካ ፓርቲ አይደለም፤ ይህን የመረዳዳት እና የመስጠት ባህልን ለማጠናከር አዋጁ እንዳስፈለገ" መግለፃቸውም ተነገረ። የእኛም የዛሬው ጽሑፋችን ከዚህ (ከአዋጁ በ441 አብላጫ ድምፅ መፅደቅ በኋላ) ወቅት ጀምሮ ያለውን ይመለከታል።

የገዳ ስርዓት (Gada system) አካልና የኦሮሞ ሕዝብ ጥንታዊ የመረዳጃ ስርዓት የሆነው ቡሳ ጎኖፋ ሥርአት የኦሮሞ ህዝብ ሰው ሰራሽም ይሁን ተፈጥሯዊ ችግር ሲያጋጥመው ችግሩን በትእግስት፣ በዘዴና በተረጋጋ ሁኔታ ለማለፍ የሚታገዝበትና እርስ በእርሱም የሚተጋገዝበት ጥንታዊ ባህል መሆኑ፤ ንቅናቄውን ማስጀመር ያስፈለገበትም ምክንያት የሕዝቡን የመረዳዳት ባህል ለማጎልበት እንደሆነ፤ ሥርአቱ ተቋማዊ መልክ እንዲኖረው ታስቦ በቢሮ ደረጃ እንደ ተቋቋመ አዲስ ዘመን ያነጋገራቸው የቢሮው ምክትል ኃላፊ አቶ ገረመው ኦሊቃ ያስረዳሉ።

> **ከገዳ ስርዓት ውስጥ በግንባር ቀደምትነት የሚነሱት የሞጋሣና ሜደቻ፣ የሲንቄና የሽምግልና የጉማ፣ የከለቻና ጫጬ፣ የቦኩና የቃሉ እንዲሁም የአያንቱ ተቋማትን መጥቀስ ይቻላል**

### ስለ “ገዳ ሥርአት“ ከጥናቶችም እናንሳ፤

በገዳ ስርአት ቀዳሚ ተጠቃሽ የሆኑት ፕሮፌሰር አስመሮም ለገሠ (ከቢቢሲ ጋር አድርገውት በነበረ ቆይታ) ኢትዮጵያ ያላትን አገር በቀል የአስተዳደር ሁኔታ ከ45 ዓመታት በፊት “ኦሮሞ ዴሞክራሲ፤ አን ኢንዲጂኒየስ አፍሪካን ፖለቲካል ሲስተም” (OROMO DEMOCRACY: An Indigenous African Political System) በሚል ርእስ ስለ ሰሩት ጥናታቸው (መጽሐፍ) "ምን ያስደነቀዎት ነገር አገኙ?" ሲባሉ "በምስራቃዊ አፍሪካ በሙሉ የዕድሜ አደረጃጀት ስርዓት አላቸው። ይህ ፖለቲካዊ ሳይሆን ማህበራዊ ስርዓት ነው። ስርዓቱም የተዘረጋው አንድ ሰው ወደ ሌላኛው በእድሜ የሚሸጋገርበትን ለመቀየስ ነው።" ነበር ያሉት። "የገዳ ስርዓት አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ለምሳሌ ስድስት አባላት ያሉትን ጉሚን ብንወስድ የመላው ቦረና ጉባኤ ማለት ሲሆን ሕግ ወሳኝና ከሁሉም በላይ የሆነ አካል ማለት ነው፤ ከባለሥልጣናቶቹም ጭምር። በጣም የሚያስገርመው፤ ውሳኔ ላይ የሚደረሰው በስምምነት ነው።" በማለትም ሀሳባቸውን ያዳብሩታል። "ስርዓት ብቻ ሳይሆን የዴሞክራሲ ቋንቋ አላቸው። የኢትዮጵያ ቋንቋ ተመራማሪዎች የዴሞክራሲ ቋንቋን ለማጥናት [ወደ'ዛ] መሄድ አለባቸው። እኔ ቋንቋውን ስለማልችል ማድረግ አልቻልም። ይህ ትልቅ ሳይንሳዊ ስርዓት መሆኑን ለማስረዳት ችያለሁም ይላሉ።

"የገዳ ስርዓት ዘመናዊ አስተዳደር ሊሆን ይችላል?" ለሚለው የቢቢሲ ጥያቄም "በደንብ፤ በአሁኑ መጽሐፌ የመጨረሻ ምዕራፍ 'ገዳ ኢን ዘ ፊውቸር ኦፍ ኦሮሞ ዴሞክራሲ' የምጠቅሰው ይህንኑ ነው።" የሚል መልስን ነበር የሰጡት። ይህም ይሄው በ"ቡሳ ጎኖፋ" እውን ሆነ። ከኢትዮጵያ ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ካገኘነው መረጃ ደግሞ ጥቂት እናክል፤

የኦሮሞ ሕዝብ እንደሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ለህልውናው ሲል በሚያከናውነው ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችና ማኅበራዊ ግንኙነቶች እንዲሁም ከአካባቢውና ከተፈጥሮ ጋር በሚያደርጋቸው መስተጋብሮች የፈጠራቸው፣ አሁንም እየፈጠራቸው የሚገኙና የማንነቱ መገለጫ የሆኑ አያሌ የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች ባለቤት ነው። [...] የገዳ ሥርዓት ከኦሮሞ ብሔር ሁለንተናዊ ሕይወትና ዕድገት ጋር በእጅጉ ተያያዥነት ያለው ሲሆን ሥርዓቱ ከቀላል የዕድገት እርከን ላይ ተነስቶ ቀስ በቀስ ውስብስብ ወደሆነ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት እያደገ የመጣ ነው። የኦሮሞ ብሔር የገዳን ሥርዓት ለረጅም ዘመናት ሲተገብረው ከመቆየቱም በላይ በሂደትም እያዳበረውና እያሳደገው ይገኛል። የገዳ ሥርዓት የኦሮሞ ብሔር ዓባላት የማንነት መገለጫ የሆኑ አንኳር ባህላዊ ገጽታዎች፣ ታሪክና እምነት እንዲሁም አገር በቀል የሆነ እውቀትን አካቶ የያዘ ጥንታዊ የዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ሥርዓት ነው። ("ቅርስ" መጽሔት፣ 2009 ዓ.ም)

ከስምንት መቶ አመታት በላይ (የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ 2009 ጥናት "ከ1522 ዓ.ም ጀምሮ በኦሮሞዎች ሲተገበር የኖረ" ካለ በኋላ "በቃል ያሉ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ሥርአቱ ከዛ በፊት ለበርካታ አመታት ሲሰራበት የነበረ ስለመሆኑ" ያስረዳል) የኦሮሞ ብሔር ዴሞክራሲያዊ የአስተዳደር ስርአት በመሆን ሲያገለግል የቆየው "የገዳ ሥርዓት ሰፊና ውስብስብ፣ በውስጡ አያሌ ንዑሳን ተቋማትንና አደረጃጀትን ያካተተ ነው። ለምሳሌ ያህል የገዳ ሥርዓት በግጭቶች ሳቢያ የተከሰቱ ችግሮችን በሂደት ለመፍታትና የተጎዳ የኅብረተሰብ ክፍልን ወይም ግለሰብን መልሶ ወደ ሰላማዊና የተረጋጋ ሕይወት ለማምጣት የሚሰሩ ተቋማት አሉት።" የሚለው የባለሥልጣኑ መጽሔት ስንቄን፣ ጉማን፣ ሞጋሳንና ሌሎችንም በማስረጃነት ያቀርባል። ለዋልታ (ዲሴምበር 2፣ 2016) ሀሳባቸውን ያካፈሉ እንግዳም “ከገዳ ስርዓት ውስጥ በግንባር ቀደምትነት የሚነሱት የሞጋሣና ሜደቻ፣ የሲንቄና የሽምግልና የጉማ፣ የከለቻና ጫጬ፣ የቦኩና የቃሉ እንዲሁም የአያንቱ ተቋማትን መጥቀስ ይቻላል።" በማለት መግለፃቸው ይታወሳል። ከአዲስ ዘመን ጋር ቆይታ ያደረጉት፣ የኦሮሚያ ቡሳ ጎኖፋ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ገረመው ኦሊቃም ይህንኑ ነው ያረጋገጡልን።

መጽሔቱ "የኦሮሞ ብሔር ባህላዊ የዲሞክራሲያዊ አስተዳደር የሆነውን የገዳን ሥርዓት ከኅዳር 19 እስከ ኅዳር 23 ቀን 2009 ዓ.ም. በአዲስ አበባ በተካሄደው አስራ አንደኛው የማይዳሰሱ ባሕላዊ ቅርሶች ጥበቃ የበይነ መንግስታት (intergovernmental) ኮሚቴ ጉባዔ ላይ በሰው ልጆች ወካይ ቅርስነት እንዲመዘገቡ ከቀረቡት 37 የማይዳሰሱ ቅርሶች መካከል አንዱ ነበር። በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሣይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) እ.ኤ.አ. በ2003 በጸደቀው የማይዳሰሱ ባሕላዊ ቅርሶች ጥበቃ ዓለም አቀፍ ሥምምነት መሠረት የገዳን ሥርዓት ለማስመዝገብ የተዘጋጀው የማስመረጫ ሰነድ አምስቱን የመመዘኛ መስፈርቶች አሟልቶ ስለመገኘቱ ዓባል አገራት ውይይት ካደረጉበት በኋላ አዎንታዊ አስተያየታቸውን በመስጠታቸው ሕዳር 21 ቀን 2009 ዓ.ም (November 30, 2016) በፋይል ቁጥር 01164 በውሳኔ ቁጥር 11.com.10. b.11 የገዳ ሥርዓት በሰው ልጆች ወካይ የማይዳሰስ ዓለም አቀፍ ቅርስነት ተመዝግቧል። የገዳ ሥርዓት በዩኔስኮ የተመዘገበ ሦስተኛው የኢትዮጵያ የማይዳሰስ ቅርስ ነው።" በማለት የተሟላ መረጃን ያቀርባል። የዋልታው እንግዳም "እኛ ኢትዮጵያዊያኖች የሰው ልጆች መገኛ፣ የጥንት ስልጣኔ ባለቤቶች ብቻ ሳንሆን የዘመናዊው የዴሞክራሲ ስርዓት መስራችም እንደሆንን አለም ለገዳ ስርዓት በሰጠው እውቅና አረጋግጦልናል።" በማለት እውቅናውን ያፀኑታል።

የኦሮሞ ህዝብ ወደ ነበረበት ቱባ ባህልና እሴቱን ጠብቆ ተቋማዊ በሆነ መንገድ እንዲረዳዳና እንዲደጋገፉ ያግዛል በሚል "ቡሳ ጎኖፋ" በአዋጅ መቋቋሙን፣ በዚሁ ስያሜም ንቅናቄ መጀመሩን፤ ድሮ የነበረውን የአደጋ ስጋት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነትን ደርቦ ወደ ስራ መግባቱን፤ የነበረውን መዋቅር ተጠቅሞም ህዝቡ ጋር ተደራሽ መሆኑን አቶ ገረመው ይናገራሉ።

ሥርዓቱ በተጠናከረ መልኩ ሲተገበር ሕዝቡ ሌሎችን ሳይጠብቅ በራሱ መንገድ ከችግሩ እንዲወጣ የሚያደርግ ሁኔታ ይፈጥራል። ‘ቡሳ ጎኖፋ’ በዋናነት ከመንግስት ከሚመደብለት በጀት በተጨማሪ ከአባላት መዋጮና ከሌሎች አካላት ድጋፍ የሚደጎም መሆኑንም ያነሱ ሲሆን፤ ‘ቡሳ ጎኖፋ’ የተሰኘው ጥንታዊ የሕዝቡ መረዳጃና ማቋቋሚያ ሥርዓትም ሕጋዊነት ባለው መልኩ እንደሚተገበርም የአዋጁን መጽደቅ ተከትሎ ያለው ሁኔታ ያስረዳል።

አቶ ገረመው እንደሚሉትም ማንኛውም ሰው አባል መሆን እንደሚችልና ለዚህም መመሪያ የተዘጋጀ መሆኑን፤ ህብረተሰቡም ባለው አቅም ሁሉ የሚሳተፍበት ንቅናቄና ተቋም እንደሆነ ገልፀዋል።

ከባለስልጣኑ የተገኘው መረጃ እንዳመለከተው፣ በኤፌዲሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ጂማ ዲልቦ የተለያዩ እርዳታዎችን ለኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ ባስረከቡበት ወቅት እንደተናገሩት፤ በተለያዩ ክልሎች ባጋጠመው ድርቅና በጦርነት ምክንያት ለተጎዱ የማህበረሰብ ክፍሎች የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ድጋፍ እንዲያደርጉ በማስተባበር ከ430 ሚሊዮን ብር በላይ በገንዘብና በዓይነት መሰብሰብ መቻሉን እና ለአማራ፣ አፋር እና ዛሬ ደግሞ ለኦሮሚያ ክልል ማስረከባቸውን ገልጸዋል። አቶ ሽመልስ አብዲሳ በኦሮሞ ህዝብና በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ስም የተሰጠውን ድጋፍ በማመስገን በህዝቡ ውስጥ የሚገኘውን የድጋፍ ባህልን ማጠናከር አስፈላጊ ነው ብለዋል። የኢትዮጵያ ህዝቦችም እርስ በዕርስ መደጋገፍ እንዳለባቸው ተናግረዋል። በገዳ ስርዓት ባህል ቡሳ ጎኖፋ የተባለ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት የተቋቋመ መሆኑን በመግለፅ ይህም ተቋም የሰው ልጆችን ችግር ለመፍታት እንደሚሰራ ገልጸዋል።

በመጨረሻም፣ ወጣቶች ስለሥርዓቱ ታሪካዊ አመጣጥና ለማኅበረሰቡ የሚሰጠው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ በተመለከተ ከአባ ገዳዎች፣ አርጋደጌቲ (ካዩት፣ ከሰሙትና በሥርዓቱ ውስጥ በማለፋቸው ስለ ገዳ ሥርዓት ታሪክና ምንነት ጠንቅቀው የሚያውቁ) እና የአገር ሽማግሌዎች የሚሰጠውን የቃል ትምህርት በአንክሮ መከታተልና መተግበር ይኖርባቸዋል፡ የሚለውን ሃሳብ እኛም እንጋራለን። የገዳ ሥርዓት በዓለም አቀፍ ደረጃ በዩኔስኮ እንዲታወቅና በሰው ልጆች ወካይ ቅርስነት የተመዘገበ ሦስተኛው የኢትዮጵያ የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርስ እንዲሆን በመንግስትና በሕዝቡ የተደረገው እልህ አስጨራሽ ጥረት ቅርሱን ጠብቆ ለትውልድ በማስተላለፉ ሂደትም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል የሚለውንም ሆነ፤ መንግስት ከሥርዓቱ ጋር በተያያዘ ሕጋዊ ማዕቀፎችን ከማውጣት በተጓዳኝ በጀት በመመደብና የቅርሱ ማከናወኛ ሥፍራዎችን የመጠበቅና መሰረተ ልማት የመገንባት፤ እንዲሁም፣ ገልማዎችን (የአባ ገዳ አዳራሽ ወይም አስተዳደራዊ ማዕከሎችን) በመስራት በቅርሱ ጥበቃ ያሳየውን ተሳትፎ አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል በሚለውም እንስማማለን። በቀጣይም አገራችን የበርካታ አኩሪ ባህሎችና መስህቦች መገኛ በመሆኗ ጠንክረን በመስራት ባህል ወጋችንን ዓለም ዓቀፉ ማህበረሰብ እንዲያውቃቸው በማድረግ የቱሪዝም ኢንዱስትሪያችንን ልናሳድግ ይገባናል የሚለውን ጥሪና ማሳሰቢያም ሆነ፤ ገዳ "... ለምን ኦሮሚያ ብቻ? በመላ አገሪቱስ ለምን ስርአተ ትምህርቱ ውስጥ ተካትቶ አይሰጥም?" የሚለውን ጥያቄ እንጋራለን። "የገዳ ሥርዓታችንም ሆነ ከእሱው አብራክ የወጣውና የ"ቡሳ ጎኖፋ" ስርአት የመቻቻልና የመከባበር፤ የመደጋገፍና የመተጋገዝ፤ የአብሮነትና አቃፊነት ባሕላችን ከመሆኑም በላይ ለህዳሴ ጉዟችንም መሠረት ነው!!" የሚለውን እናጸናለን። ስንብታችንም "ቡሳ ጎኖፋ ለአገርና ለህዝብ በሚጠቅም መልኩ በስፋት ይሰራል" በሚለው የኦሮሚያ ቡሳ ጎኖፋ ምክትል ኃላፊ አቶ ገረመው ኦሊቃ አስተያየት ነው።

# ወጣቱ በዚህ ወቅት

**አስናቀ ፀጋዬ**



ወይዘሪት ሌሲ በላይ፣

ወጣት ትኩስ ሃይል ነው። ኢትዮጵያ ደግሞ ይህ ትኩስ ሃይል በብዛት የሚገኝባት አገር ናት። ይህ ሃይል ጥቅም ላይ እስካልዋለ ድረስ ግን ቁጥር ብቻ ነው የሚሆነው። የአገር እድገት ሲታሰብም ወጣቱን በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በስፋት ማሳተፍ ያስፈልጋል። ለወጣቱ የስራ እድል መፍጠርም የግድ ይላል።

ይህን ማድረግ ካልተቻለ ግን ወጣቱ ሃይል ለማህበረሰብ፣ ለአገርና ለመንግስት መልሶ ስጋት መሆኑ አይቀርም። በተለይ ደግሞ የወጣት ስራ አጥ ቁጥር ማሻቀብ ቁጣን ቀስቅሶ በመንግስት ላይ ድንጋይ ለመወርወር ይጋብዛል። ይህ ትኩስ ሃይል በአግባቡ ስራ ላይ ባለመዋሉ አገሪቷንም በርካታ ገቢ ያሳጣታል። ለዚህም ነው በወጣቶች ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት አስፈላጊ ነው የሚባለው።

በአሁኑ ጊዜ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየአመቱ ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል። ይህ ሁሉ የተማረ ወጣት ታዲያ ሁሉም ተቀጥሮ ይሰራል ማለት አይደለም። ተቀጥሮ ለመስራት እንኳን ውድድሩ ቀላል አይሆንም። ከዚህ አኳያ ወጣቱ በራሱ ስራን ፈጥሮ መስራት መልመድ አለበት። መንግስትም ወጣቶች የራሳቸውን ስራ ፈጥረው እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይኖርበታል።

የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ይታወቃል። ህዝቡ በጦርነት ውስጥ አልፏል። ድርቅ፣ መፈናቀል፣ ሞትና የቤት ንብረት ውድመት ተከስቷል። የኑሮ ውድነቱ ጨምሯል። የፖለቲካ ትኩሳቱ ጦዟል። አገሪቷም በፈተና ውስጥ ትገኛለች። ወጣቱ ደግሞ የዚህ ፈተና አንዱ አካል ነውና በዚህ ወቅት ከወጣቱ ብዙ ነገር ይጠበቃል። ለመሆኑ በዚህ የፈተና ወቅት ከወጣቱ ምን ይጠበቃል? ፈተናዎችንስ እንዴት ማለፍ ይኖርበታል?

ወይዘሪት ሌሲ በላይ ኮንሰርቲየም ዩዝ ዴቨሎፕመንት ኦርጋናይዜሽን ኢን ኢትዮጵያ የተሰኘ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት ድርጅቱ ከአምስት ክልሎች ማለትም አዲስ አበባ፣ አማራ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች፣ ኦሮሚያና ትግራይ በተውጣጡ የወጣት ድርጅቶች በ2005 ዓ.ም ተቋቁሟል።

በ2005 ዓ.ም በወጣቶች ስነ ተዋልዶ ጤና ላይ ያተኮረ ሲምፖዚየም በባህርዳር ከተማ ተካሂዶ ነበር። በዚሁ ሲምፖዚየም ላይ በአብዛኛው የሚወራው ስለወጣትና ስነ ተዋልዶ ጤና ነበር። ሆኖም በዚህ ሲምፖዚየም ላይ ወጣቱን ህብረተሰብ ወክሎ የሚናገር አካል አልነበረም። ከዚህ ይልቅ ሌሎች ሰዎች ነበሩ ስለወጣቶች ሲያወሩ የነበሩት።

በጊዜው በሲምፖዚየሙ ላይ የተገኙት ወጣቶች ስለኛ ለምን እናንተ ትናገራላችሁ ስለኛው እኛው እንናነገር በሚል አነሳሽነት ድርጅቱ ሊቋቋም ችሏል። የድርጅቱ ዋነኛ አላማውም የወጣት ህብረት በመፍጠር ወጣት መርና ወጣት ተኮር ድርጅቶች አንድ ላይ ሆነው በተለያዩ ወደ አስራ ሶስት ጉዳዮች ላይ በጋራ ይሰራሉ።

ከነዚህ ጉዳዮች ውስጥም የስነ ተዋልዶ ጤና፣ ወጣቶችን ማብቃት፣ ስራ አጥነትና ስደት ይገኙበታል። ድርጅቱ በዋናነት የሚሰራው ግን በጋራ መስራትን መፍጠርና እነዚህን ወጣት ተኮር ድርጅቶችን የማብቃትና ማበረታታት ነው።

እንደ ወይዘሪት ሌሲ ገለፃ የድርጅቱ ዋነኛ ስራ ትግበራ ላይ ሳይሆን ወጣት ተኮር ድርጅቶችን ወደ አንድ የማምጣትና እነርሱ የሚሰሩትን ሥራ ወደ ፖሊሲ ቀይሮ የማስረፅ ነው። ከዚህ አንፃር በወጣቶች ህብረት ምክር ቤት በኩል በተለይ በአገራዊ ምክክር መድረኩ ወጣቶች በምን መልኩ መሳተፍ እንዳለባቸውና ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው አብሮ በመወያየትና ለወጣቱ ድምፅ በመሆን ስራዎችን እየሰራ ይገኛል።

ድርጅቱ በወጣቱ በኩል ያለውን ጉዳይ ለመሸፈንና ድምፅ ለማሰማት ብሎም በጋራ ለመስራት ባሉ ፕሮግራሞች ላይ ይካፈላል። የድርጅቱ አባል የሆኑ ወጣቶችን በተለያዩ መድረኮች በመላክና ድምፃቸውን እንዲያሰሙ በማድረግ የራሳቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱም እያደረገም ይገኛል።

ድርጅቱ ከዚህ በፊት በ2012 ዓ.ም ምርጫ ሊካሄድ ሲል ፕሮጀክቶችን ቀርጾ የተለያዩ ውይይቶች በወጣቶች በኩል ይካሄድ ነበር። ወጣቱ እንዴት አድርጎ ድምፁን ማሰማት እንዳለበትና በተለይ ወጣት ሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎ በዲሞክራሲ ላይ ያለው አስተዋጽኦ ለማሳደግ ሴቶች ምን ማድረግ እንዳለባቸውና ግጭትን እንዴት ማስወገድ እንደሚኖርባቸው የተለያዩ ርእሶችን በማንሳት ወጣቶች ውይይት ሲያካሂዱ ነበር።

**ሁሉም ወጣት ባለበት ቦታ ላይና በተሰማራበት የሙያ መስክ ትክክለኛውን ነገር ማድረግ ይጠበቅበታል። አስፈላጊ ካልሆኑ ጉዳዮች ራሱን በማራቅ በሚጠቅሙት ላይ ብቻ ማተኮር ይገባዋል። የችግሮች ምንጭ ላይ አተኩሮ መስራት ከተቻለም ዘለቄታ ያለው መፍትሄ ማምጣት ይቻላል**

ይህ ውይይት እንዲሰረፅና በአመራር ላይ ያሉ ሰዎች በምርጫና የተለያዩ ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ የማድረግ፣ ወጣቶች ራሳቸውን በምርጫ እጩ ተወዳዳሪ አድርገው እንዲቀርቡ የማድረግና ይህንን እንደሚችሉ የማሳወቅ ስራዎችንም ድርጅቱ ሲሰራ ቆይቷል።

አሁንም በተመሳሳይ ድርጅቱ ከወቅታዊ አገራዊ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ወጣቶች የራሳችን ድርሻ ነው ብለው ግጭቶችን በተለያዩ መንገድ ማስወገድ እንዲችሉና ይህንኑ ድምፃቸውን እንዲያሰሙ ወደ አንድ የማምጣትና የማቀናጀት ስራዎችን እየሰራ ይገኛል። በተለይ ደግሞ ወጣት ተኮር ከሆኑ ድርጅቶች ጋር አጋርነት በመፍጠር በወቅታዊ አገራዊ ሁኔታ ላይ የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የማብቃት ስራዎችንም እያከናወነ ነው።

በአገራዊ የምክክር መድረኩ ላይ ወጣቶች ተሳታፊ ሆነው ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡ ድርጅቱ ከወጣቶች ምክር ቤት ጋር በተለያዩ መድረኮች ላይ በተደጋጋሚ ተገናኝቶ ተወያይቷል። በአገራዊ ምክክሩ የድርጅቱና የወጣቱ ድርሻ ምን እንደሆነም ጠይቋል። በወጣቶች ዙሪያ የሚሰሩ ድርጅቶች በአገራዊ ምክክሩ በምን መልኩ መሳተፍ እንደሚችሉም አውርቷል። ጉዳዩ አገር አቀፍ በመሆኑ በየአካባቢው ያሉትን ወጣቶች በአገራዊ ምክክሩ ተደራሽ ማድረግ ይቻላል።

ከዚህ አንፃር ድርጅቱ ከአገራዊ የምክክር መድረኩ ጋር በተያያዘ ወጣቶች ተሳታፊ ሆነው ሃሳባቸውን እንዲያካፍሉ እንደ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል። ወጣቶች እነሱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑም ያነቃቃል። ሁኔታዎችንም ያመቻቻል።

ወይዘሪት ሌሲ እንደሚሉት ከሰሞኑ ከወቅታዊ አገራዊ ጉዳይ ጋር በተገናኘ ለአባል የወጣት ተኮር ድርጅቶች በጉትጎታና ተሟጋችነት ዙሪያ ሥልጠናዎች ሲሰጡ ነበር። ወጣቶች ፀብና አምባጓሮ አስነስተው ፍላጎታቸውን ለማሳካት ከመጣር ይልቅ ከግጭት የፀዱ መንገዶችን በመከተል ድምፃቸውን ማሰማት እንደሚችሉ ከዚህ ስልጠና ተምረዋል።

በሰላማዊ መንገድ ወጣቶች ድምፃቸውን በማሰማት የመንግስትን ፖሊሲ ማስቀየርና መንግስት ላይም ተፅእኖ ማሳደር እንደሚችሉም ተረድተዋል። የጉትጎታና ሙግት ጉዳይ ደግሞ በኢትዮጵያ ብዙም ያልታወቀ በመሆኑ ሁሉም አባል የወጣት ድርጅቶች ስልጠናውን እንዲያገኙ ተደርጓል።

በሌላ በኩል ደግሞ የድርጅቱ ዋነኛ ራዕይ ወጣቱ የግጭቶች ሰለባና የጥፋት ሃይሎች መሳሪያ እንዳይሆን በመሆኑ በዚህ ላይ ትልቅ ትኩረት አድርጎ እየሰራ ይገኛል። በተለይ ደግሞ ድርጅቱ ራሱን የሚያውቅና በራሱ መወሰን የሚችል ወጣት እንዲፈጠር አበክሮ ይሰራል።

ይህ ስራ ሲሰራ ታዲያ ወጣቱን ወደ ግጭትና ለጥፋት ሃይሎች መጠቀሚያ የሚያመሩት ምክንያቶችን መለየት ያስፈልጋል። ምክንያቶቹ ግን በርካቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ለአብነትም ስራ አጥነትን መጥቀስ ይቻላል። ወጣቱ ስራ አጥ ባይሆን ኖሮ የማንም መጠቀሚያ አይሆንም። ገንዘብ ለማግኘትም ሆነ በተለያዩ ጉዳዮች ምክንያት ወጣቶች የነዚህ የጥፋት ሃይሎች መጠቀሚያ ሲሆንም ይታያል።

ከዚህ አንፃር ድርጅቱ ወጣቱ የጥፋት ሃይሎች መጠቀሚያ ወደሆነበት መነሻ ምክንያቶቹ እየሄደ በጉዳዩ ላይ ፕሮጀክት ቀርጾ እነዚህ ችግሮች እንዳይፈጠሩ በራሱም ሆነ በአባል ድርጅቶቹ በኩል ይሰራባቸዋል። ራሱን የሚያውቅ፣ ድንጋይ የማያነሳና ለመብቱ የሚከራከር ወጣት እንዲፈጠርም ይሰራል።

ከወጣቶች ጋር በተገናኘ ድርጅቱ ለሚያከናውናቸው ስራዎች ሁሉ ዋነኛ ባለድርሻ አካል መንግስት ነው። በተለይ ደግሞ ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመሆን የተለያዩ ስራዎች በጋራ ይሰራሉ። በዚህም የወጣቶች ካውንስል እየተቋቋመም ነበር። ካውንስሉ ሲቋቋም ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በመቀራረብ ወጣቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን በማነሳት በጋራ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። በጤና ዘርፍም ከጤና ሚንስቴር ጋር ተመሳሳይ ስራዎች ተሰርተዋል።

ከዚህ ባለፈ ሁሉም ወጣት ባለበት ቦታ ላይና በተሰማራበት የሙያ መስክ ትክክለኛውን ነገር ማድረግ ይጠበቅበታል። አስፈላጊ ካልሆኑ ጉዳዮች ራሱን በማራቅ በሚጠቅሙት ላይ ብቻ ማተኮር ይገባዋል። የችግሮች ምንጭ ላይ አተኩሮ መስራት ከተቻለም ዘለቄታ ያለው መፍትሄ ማምጣት ይቻላል።

አልያ ግን አብዛኛውን ጊዜ የችግሮች ውጤት ላይ ቢሰራም ነገም መልሶ ችግሩ ሊከሰት ስለሚችል የችግሩ ምንጭ ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ይሻላል። ይህም ኋላ ለሚመጣው ትውልድ መንገድ ለመጥረግ ያስችላል። በአገር ላይም ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት ያስችላል።

## የምድር በረከት

# ተስፋ የተጣለበት የድንጋይ ከሰል ሀብት

**መላኩ ኤርሴ**

ዘመናዊ የአኗኗር ዘዴ ከኤሌክትሪክ ኃይል ውጭ ሊታሰብ አይችልም። ቤቶች፣ ጎዳናዎች፣ ኢንዱስትሪዎች ብርሃን እና ሙቀት የሚያገኙት ከኤሌክትሪክ ነው። በቤት በቢሮዎች እና በፋብሪካዎች ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ቁሶችንና ማሽነሪዎችን ያለ ኤሌክትሪክ ማሰብ ከባድ ነው። የኤሌክትሪክ ኃይል ከተለያዩ ምንጮች ሊገኝ የሚችል ሲሆን፤ ከኤሌክትሪክ ኃይል ምንጮች ትልቁ የድንጋይ ከሰል ነው።

የድንጋይ ከሰል መጠቀም ለአየር ንብረት ለውጥ አስተዋጽኦ ስለሚያበረክት ከኃይል ምንጭነት ለማስወጣት ጥረቶች ቢደረጉም ዛሬም የዓለም ትልቁ የኤሌክትሪክ ኃይል ምንጭ ሆኖ ቀጥሏል። የዛሬ ሶስት ዓመት ገደማ የወጡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ የድንጋይ ከሰል በአሁኑ ጊዜ በዓለም 36 በመቶ ድርሻ ያለው ትልቁ የኤሌክትሪክ ኃይል ምንጭ ሆኖ ቀጥሏል። እንዲሁም ወደ ኃይል ለመቀየር በአንፃራዊነት ቀላል እና እርካሽ በመሆኑ አገራት ዛሬም የድንጋይ ከሰልን መጠቀማቸውን ቀጥለዋል።

ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ ሊሆን የሚችል የድንጋይ ከሰል የታደለች አገር ብትሆንም ይህንን ሀብት በሚገባ ሳትጠቀም ቆይታለች። በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የድንጋይ ከሰል ፍላጎት ለማሟላት ከውጭ አገራት ስታስገባ ቆይታለች። ከፍተኛ ወጪ በማውጣት የድንጋይ ከሰል ከውጭ አገራት እንደምታስገባ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህም በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ጫና ሲያሳድር ቆይቷል። ይህንን ሁኔታ ለመቀየር ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ የከሰል ድንጋይን በአገር ውስጥ ለማምረት እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል።

በቅርቡ 6ኛው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 1ኛ ዓመት የሥራ ዘመን ዘጠነኛ መደበኛ ጉባኤ የማዕድን ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት አዳምጧል። በማዕድን ዘርፍ በተሰሩ ሥራዎች ዙሪያ የተለያዩ ጥያቄዎችና ማብራሪያዎችን ተጠይቀዋል። በዚህ ወቅት በምክር ቤቱ ሰፊ የመነጋገሪያ ርዕሰ ጉዳይ ከነበሩት አንዱ የድንጋይ ከሰል ልማት ጋር ተያይዘው ያሉ ጉዳዮች ናቸው። የድንጋይ ከሰል ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ግንባታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፣ ለኢንዱስትሪው ስኬታማነት ወሳኝ የሆኑ መሰረተ ልማቶች ማለትም ኤሌክትሪክ ኃይል፣ ውሃና መንገድ የመሳሰሉ መሰረተ ልማቶች ለፋብሪካዎቹ ስኬታማነት ወሳኝ በመሆናቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ምን ይመስላል፣ የድንጋይ ከሰል በሚመረትባቸው አካባቢዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያደርስ አምራቾቹ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ምን አይነት ክትትል እና ድጋፍ እያደረገ ነው፤ ማዕድኑ በሚመረትባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ህዝቦች ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ምን ሥራዎች እየተሠሩ ነው የሚሉ ጥያቄዎች እና ማብራሪያዎች ተነስተዋል።

የሚኒስቴሩ አመራሮችም ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል። የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ኡማ በሰጡት ማብራሪያ፤ ሚኒስትር አቶ ታከለ ኡማ፤ ባለፉት ዓመታት የኢትዮጵያ ድንጋይ ከሰል ጥራት ይጎድለዋል፣ የአመድ ይዘቱ ከፍተኛ ነው፣ የሰልፈር ይዘቱ ከፍተኛ ነው፣ የእርጥበት መጠኑ ከፍተኛ በሚል የኢትዮጵያ ድንጋይ ከሰል ለኢትዮጵያ ስለማይጠቅም ከውጭ ይግባ የሚል ትርክት ነው የነበረው። በዚህ መሰረትም ለብዙ ዓመታት ኢትዮጵያ ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሪ በማውጣት ድንጋይ ከሰል ከውጭ አገራት ስታስገባ ቆይታለች። ባለፉት ዓመታት ለሲሚንቶ እና ለሌሎች ፋብሪካዎች ግብዓት የሚሆን የድንጋይ ከሰል በዓመት ከ300 ሚሊየን ዶላር በላይ ወጪ እያደረገች ለፋብሪካዎች የሚያገለግል የከሰል ድንጋይ ከውጭ አገራት ስታስገባ ቆይታለች።

ይህንን ሁኔታ ለመቀየር በኢኮኖሚ እና ፖለቲካ ሪፎርሙ ከአምስቱ የብዝሃ ኢኮኖሚ ግንባታ ውስጥ ማዕድን አንዱ ምሰሶ እንዲሆን ተደርጓል። በአገሪቱ ውስጥ ያሉ ማዕድኖችን ማስጠናት፣ ማወቅ እና መጠቀም አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት በለውጡ ማግስት ነው የተጀመረው። በዚህ ትልቅ ትኩረት ከተሰጣቸው ማዕድኖች አንዱ የድንጋይ ከሰል ነው ይላሉ ሚኒስትሩ።



የኢትዮጵያ ድንጋይ ከሰል ጥራትን በተመለከተ የነበረውን ትርክት ለመቀየር ሥራዎች መሠራታቸውን የሚያነሱት ኢንጂነር ታከለ፤ የኢትዮጵያ ድንጋይ ከሰል ጥራት ለማወቅ ቱርክ፣ ደቡብ አፍሪካ እና ቻይና በመላክ የማወቅ ሥራ ተሰርቷል ይላሉ። በሶስቱም አገራት ላቦራቶሪዎች ውስጥ የተረጋገጠው ኢትዮጵያ ከውጭ አገራት ከምታስገባቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው የድንጋይ ከሰል የማቃጠል አቅሙ የተሻለ መሆኑን ማረጋገጥ መቻሉን ጠቁመዋል።

ከውጭ የሚገባው የድንጋይ ከሰል የማቃጠል አቅሙ አምስት ሺ ካሎሪክ አቅም ያለው ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ግን ከስድስት ሺ ኪሎ ዋት አቅም በላይ ያለው መሆኑ ተረጋግጧል። ይህም የሚያሳየው የኢትዮጵያ ድንጋይ ከሰል ኢትዮጵያ ከውጭ ከምታስገባቸው ድንጋይ ከሰሎች በላይ ሀይል የመስጠት አቅም ያለው እና አነስተኛ ጭስ የሚያመነጭ መሆኑን ነው።

እንደ ኢንጂነር ታከለ ማብራሪያ፤ ይህ ከተረጋገጠ በኋላ ስምንት ፋብሪካዎች ድንጋይ ከሰል ማምረት እንዲጀምሩ መንግሥት 25 ሚሊየን ዶላር ለኩባንያዎቹ ሰጥቷቸዋል። መንግሥት ካለው የውጭ ምንዛሪ ክምችት አውጥቶ የሰጠው ፋብሪካዎቹ በፍጥነት ወደ ሥራ መግባት እንዲችሉ ነው። በዚሁ መሰረት አንዳንዶቹ ወደ ሥራ ለመግባት ጥሩ እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው። አንዳንዶች የማሽን ግዢ ፈጽመዋል፣ አንዳንዶቹ ጥናታቸውን ጨርሰዋል፣ አንዳንዶቹ የላቦራቶሪ ጉዳዮችን ጨርሰዋል።

በትብብር መሥራት ከተቻለ በቀጣይ ጊዜ ከሰል ከውጭ አገራት ማስገባት ይቆማል። አገሪቱ የድንጋይ ከሰል ከውጭ ማስገባት ስታቆም ለተወሰኑ ወራት የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ሊቸገሩ እንደሚችሉ እና የሲሚንቶ ምርት ሊቀንስ ቢችልም የአገር ውስጥ ድንጋይ ከሰል ጥቅም ላይ ማዋል ይገባል ብለዋል።

የአገሪቱ የከሰል ድንጋይ ፋላጎት ሰባት ነጥብ ስምንት ሚሊየን ቶን የከሰል ድንጋይ ሲሆን፤ በቀጣይ ጊዜያት ኢትዮጵያ ውስጥ የድንጋይ ከሰል ማምረት ይጀምራሉ ተብለው የሚጠበቁ የድንጋይ ከሰል ፋብሪካዎች የማምረት አቅም ግን አራት ነጥብ አምስት ሚሊየን ቶን መሆኑን ነው ያነሱት። በአገር ውስጥ የሚመረተው የድንጋይ ከሰል የሁሉንም ፋብሪካዎች ፍላጎት ላያሟሉ እንደሚችሉ ጠቁመዋል። የድንጋይ ከሰል አምራቾቹ ለጊዜው የሲሚንቶ ፋብሪካዎችን ፍላጎት እንዲያሟላ ጥረት ይደረጋል። በቀጣይ ደግሞ የማዳበሪያ ፋብሪካዎች የከሰል ድንጋይ ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችል የድንጋይ ከሰል በአገር ውስጥ ለማምረት ጥረት እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

ድንጋይ ከሰልን በአገር ውስጥ ለማምረት እንቅስቃሴ መጀመሩ ትርክቶቹ እየተቀየሩ መሆናቸውን አመላካች ቢሆንም፤ ሆኖም እነዚህ የድንጋይ ከሰል የሚመረቱባቸው ክልሎች የየራሳቸው ጥያቄዎች አሏቸው። የድንጋይ ከሰሉ ጥቅም ላይ እየዋለ ሲሄድ የድንጋይ ከሰል የሚመረትባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ህዝቦች ተጠቃሚ እየሆኑ እንደሚሄዱም ጠቁመዋል። በአሁኑ ወቅት ግን ምርት ላይ አልተደረሰም። ምርት ላይ ስላልተደረሰ ብዙ ብዢታዎች አሉ። አንዳንድ ክልሎች ከፋብሪካዎቹ እስከ 30 በመቶ የክልሉ ወጣቶች እንዲይዙ የመፈለግ አዝማሚያ አለ። ብዙ ፋብሪካዎች በሌሉባቸው እና ገና ባለሙ ክልሎች ግን የ30 በመቶ ጥያቄ ማንሳት ተገቢ አይደለም ብለዋል። ክልሎች ከምንም በላይ በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሃብቶችን መሳብ ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው። ከጅምሩ ከፍተኛ ድርሻ ለመያዝ የሚደረገው ሩጫ ባለሃብቶች ወደ ሥራ እንዳይገቡ የሚያደርግ መሆኑንም አብራርተዋል።

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሁለት ኩባንያዎች የፋብሪካ ግንባታ ላይ መሆናቸውን የጠቆሙት አቶ ታከለ፤ በሚያመርቱ ባለሃብቶች የወጣቶችን ችግር መፍታት ይቻላል። ሌሎች ክልሎችም በተመሳሳይ ይሰራል። ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ የድንጋይ ከሰል ከውጭ እንደማይገባ የጠቆሙት ኢንጂነር ታከለ፤ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በአገር የድንጋይ ከሰል እየተጠቀሙ ማምረት ይጀምራሉ።

አገሪቱ የከሰል ድንጋይን ጨምሮ ከሌሎች ማዕድናት ማግኘት ያለባትን ጥቅም ማግኘት እንድትችል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ ጠቁመዋል። ለድንጋይ ከሰል ልማትና ስኬታማነት ወሳኝ የሆኑ መሰረተ ልማቶች ማለትም ኤሌክትሪክ ሀይል፣ ውሃና መንገድ የመሳሰሉ መሰረተ ልማቶች ለፋብሪካዎቹ ስኬታማነት ወሳኝ በመሆናቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት መሥራት ይገባል።

የድንጋይ ከሰል ልማት በጥንቃቄ ካልተያዘ የእርሻ ቦታ፣ የመጠጥ ውሃ እና ብዝሃ ሕይወት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ በመሆናቸው በማህበረሰቡ ዘንድ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ፤ በዘርፉ የተሰማሩና የሚሰማሩ ባለሃብቶች ከስራቸው ጎን ለጎን አካባቢውን እንዲያለሙና አሉታዊ ተፅዕኖዎችን እንዲከላከሉ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ እንደሚገባም ተጠቁሟል።

በአገር ውስጥ የሚመረተው የከሰል ድንጋይ ደረጃው የተለያየ በመሆኑ የጥራቱ ደረጃ ቢቀመጥለት ለተጠቃሚውና ለዋጋ ተመን የሚጠቅም በመሆኑ የማዕድናትን ጥራት ደረጃ ከመወሰን አንጻር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በትኩረት ሊሠራ እንደሚገባ የጠቆሙት አባላቱ፤ የአካባቢውን ማህበረሰብ እና ወጣቱን ከድንጋይ ከሰል አምራች ባለሃብቶች ጋር በማስተሳሰር የሥራ እድል ከመፍጠር አንጻር አሰራርን በግልጽ ማስቀመጥ ተገቢ መሆኑንም አመላክተዋል።

አንዳንድ ፋብሪካዎች በ2014 ከውጭ የሚገቡ የድንጋይ ከሰል ምርቶችን በአገር ውስጥ ለመተካት የድንጋይ ከሰል አምራቾች ፈቃድ የተሰጣቸው ቢሆንም እስካሁን ይህ ነው የሚባል እንቅስቃሴ ባለመታየቱ የድንጋይ ከሰሉ ይመረትባቸዋል ተብለው ከሚጠበቁ አካባቢዎች ማህበረሰብ ቅሬታዎች እየተነሱ እንደሆነ የጠቆሙት አባላቱ ቢሆንም ወደ ተግባር ከማስገባት ረገድ ያለው እንቅስቃሴ ዝቅተኛ ነው። ኩባንያዎች የድንጋይ ከሰል ወደማምረት እንዲገቡ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኩባንያዎቹን ወደ ሥራ ለማስገባት በትኩረት ሊሠራ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

የድንጋይ ከሰልን ጨምሮ ሌሎች ማዕድናት በሚመረቱበት አካባቢ የአድሎዊነት፣ የአለመረጋጋት እና የግጭት መንስዔ እንዳይሆኑ ተቋሙ ኃላፊነት መውሰድ እንዳለበት የጠቆሙት የምክር ቤቱ አባላት የተቋሙ የማዕድን ጥናቶች በዳታ ቤዝ መያዝ እንዳለባቸው እና ዓለም-አቀፋዊ ተወዳዳሪ ሊሆኑ እንዲሚገባም አመላክተዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤ ሰሞኑን በዳውሮ ዞን የመስክ ምልከታ ያካሄደ ሲሆን ቡድን በዞኑ የሚገኙ የድንጋይ ከሰል ማምረቻዎችን ተዘዋውሮ ከዞኑ አመራሮች፣ ከአካባቢው ማኅበረሰብ እና ከድንጋይ ከሰል አምራቾች ጋር ተወያይተዋል።

የዳውሮ ዞን የድንጋይ ከሰል ሲመረት ለአካባቢ ጥበቃ ትኩረት ከመስጠት ጎን ለጎን ለአካባቢው ማኅበረሰብ አገልግሎት መስጠት የሚችል ጤና ጣቢያ፣ ትምህርት ቤት፣ መንገድ፣ ንጹሕ የመጠጥ ውኃ እና የመሳሰሉትን መሠረተ-ልማቶች በመሥራት፤ የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንደሚገባም አስገንዝበዋል። በአካባቢው የከሰል ድንጋይ የማምረት ሥራ ሲጀመር የአካባቢውን ማኅበረሰብ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከሚሠራው ሥራ በተጨማሪ፣ ቴክኖሎጂን ለማሸጋገር መጣር እንዳለበት የምክር ቤቱ አባላት መጠቆማቸውን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በፌስቡክ ገጹ አስፍሯል።

በምክትል ማዕረግ የዳውሮ ዞን ዋና አስተዳዳሪ ክቡር ምትኩ መኩሪያ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የድንጋይ ከሰል እስካሁን ያልተሠራበት አዲስ ዘርፍ በመሆኑ የአሠራር መመሪያ (Guideline) ስለሌለው፣ ዘርፉን ለመምራት መቸገራቸውን ገልጸዋል። የፌዴራል መንግሥት ጥናት አካሂዶ ግልጽ የአሠራር መመሪያ ማዘጋጀት እንዳለበትም ጠቁመዋል። ዋና አስተዳዳሪው አክለውም፤ በፌዴራል መንግሥት በኩል ማዕድናትን የሚመለከቱ ሕጎችን ለማውጣት በሚደረገው ውይይት፣ በየደረጃው ያለውን አመራር እና ሕዝብ ማወያየት ቢቻል፣ በዘርፉ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚረዳ ግብዓት ይገኛል ብለዋል።

ለማምረት ፈቃድ የተሰጣቸው የድንጋይ ከሰል አምራቾች በውላቸው መሠረት ወደ ሥራ እንዲገቡ የወረዳው እና የዞኑ አመራር መሥራት እንዳለበትም አሳስበው፤ የፌዴራል መንግሥትም ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት ዋና አስተዳዳሪው ጨምረው አሳስበዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ጦርነት ጀግና የለውም

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

የሰፈራችን እድር ለፋፊ ጋሽ ቢራራ ትላንት ማለዳ ለአባቴ እንድነግረው መልዕክት ልከውኝ ነበር። ዛሬ ጠዋት መንገድ አግኝተውኝ “ለአባትህ ነገርከው እንዴ” ቢሉኝ ነው ስበር ቤት የመጣሁት። ቤት ስገባ አባቴ ዜና እያደመጠ ነበር። በእኛ ቤት ህግ ውስጥ አባቴ ዜና እያደመጠ ማውራት አይፈቀድም። ጉዳይ ያለው ሰው አባቴን ለማግኘት ዜናውን እስኪጨርስ መጠበቅ ግዴታ አለበት። እኔም በገዛ አባቴ ላይ መብት ተነፍጌ የገዛ አባቴን መጠበቅ ጀመርኩ። ከተለያየ ሰው የተላኩት ለአባቴ ያልነገርኩት አንድ መዐት መልዕክት ልቤ ውስጥ አለ።

ጊዜአቸው ያለፈ፣ ሰሚ ያጡ መልእክቶች። ይሄኛውን ግን ጠብቄም ቢሆን መናገር አለብኝ ያለዛ ጋሽ ቢራራ መታወቂያ ለማውጣትም ሆነ ለማደስ እዛች ቀበሌ ቤት ድርሽ አያደርጉኝም..ሲበዛ ቂመኛ ናቸው። የዛሬ አመት የጠፋ የቀበሌ መታወቂያዬን ላወጣ ሄጄ የሆንኩትን አረሳውም..ሁለት ጊዜ ለአባቴ መልዕክት ልከውኝ ረስቼው ሳላደርስ ቀርቼ ነበር። ያን እንደ ቂም ቆጥረው ሳምንት ሙሉ ደጅ አስጠንተውኛል። አሁን..አሁን አድገን ገባን እንጂ በፊት ቀበሌ ቤቱ የእሳቸው ይመስለን ነበር።

ፊት እያዩ፣ ውለታ እየቆጠሩ ነበር ሲያስተናግዱ የነበሩት። ይሄ ብቻ አይደለም የመንደሩ እድር ለፋፊ ስለሆኑ ቂም የያዙባቸው ሰው ቤት ሀዘን ሲኖር ከልባቸው ጡሩንባ አይነፉም፣ ድንኳንና፣ የለቅሶ ቤት እቃ ሲሰጡ እንኳን ያዳላሉ ይባላል። በዛ ላይ መታወቂያዬ ጊዜው አልፏል መታደስ አለበት..ታዲያ የጋሽ ቢራራን መልዕክት ይዤ ወደ አባቴ ብሮጥ ምን ይገርማል ትላላችሁ?

ቤት ስደርስ አባቴ ሪሞቱን በእጁ እንደጨበጠ አይኑን ቴሌቪዥኑ ላይ ተክሏል። ያ ሪሞት መቼ ከአባቴ እጅ እንደሚወጣ አላውቅም። ጠዋት ከእንቅልፌ ስነቃ ከነሪሞት እዛች ዘወትር የሚቀመጥባት ለወገቤ ትመቸኛለች የሚላት ባለመደገፊያ ሶፋ ላይ አየዋለው። ከሰዐትም ማታም እንዲህ እንደ አሁኑ ተንጦልጦዬ ቤት ስመጣ ከነሪሞቱ እዛችው ጠዋት የተቀመጠባት ሶፋ ላይ አገኘዋለው። እኔ እናቴና ታናሽ እህቴ በየፊናችን እንብሰለሰላለን። እናቴ ማዕድ ቤት..እህቴ ከሶፋው ላይ ከነጫማዋ፣ እኔ አንዴ በርጩማው ላይ አንዴ አግዳሚው ላይ።

አባቴ በሚሰማው የሩሲያና ዩክሬን ጦርነት እህህ ይላል። ዝምታ በዋጠው በዚያ ቤት ነው” “የአባቴ እህህ እዬዬ ነበር።

አይኑን ከቴሌቪዥኑ ላይ ሳይነቀል ‹እኚህን ሰዎች አስታራቂ ጠፋ አይደል?

የአባቴን ድምጽ ተከትዬ ‹ማነው ይሄ..የሩሲያው ጠቅላይ ሚኒስተር?

‹ፑቲን ማለትህ ነው..ደሞ ጠቅላይ ሚኒስተር አይደለም ፕሬዚዳንት ነው› አባቴ በኔ መሳሳት ውስጥ ጣልቃ ገባ።

‹ግን ጀግና ነው..ኃያላኖቹን እኮ አንቀጠቀጣቸው› አልኩ።

‹የጦርነት ጀግና የለውም። ጀግና ሰላም ውስጥ ነው የሚፈጠረው። ችግራችን ጀብደኝነትን ነውጥ ውስጥ መፈለጋችን ነው። አገራችን ለምን ድሀ የሆነች ይመስለሀል? ጀግኖቿ ሁሉ በጦርነት ውስጥ የተፈጠሩ ስለሆነ ነው። አገር የሰላም አንባሳደር፣ የሰላም አለቃ ነው የሚያስፈልጋት። አገር የይቅርታና የመቻቻል እውቀት ነው የሚያስፈልጋት። አንተም ሆንክ ታሪክህ ጀግንነታችሁን ሰላምና መረጋጋት ውስጥ ፈልጉት።

ምን እንደምል ጠፍቶኝ ዝም አልኩ። ለስሙ እኮ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነኝ፣ ለስሙ እኮ የት ይደርሳል የተባለልኝ ነኝ። አባቴ ልቡን ቀልቡን ለዜናው ሰጥቶ ዝም አለ።

‹እኛጋ አይድረሱብን እንጂ እነሱስ እንደብጥርጥራቸው› ስትል እናቴን ከወደ ጓዳ ሰማኋት። በእናቴ ንግግር አባቴ ዝም አላለም ዳግመኛ አንደበቱን ፈታ።

‹ምን ትያለሽ? ጦርነቱ እኮ በቆመህ ጠብቀኝ አይደለም..በባላስቲክ ሚሳኤል ነው›

‹ቢሆንስ ታዲያ! የት አባታቸው ያገኙናል..

‹አሁንስ መች አጡን፣ እያገኙን እኮ ነው..የኑሮ መወደዱ፣ የታሪፍ ጭማሪው በማን የመጣ መሰለሽ በነሱ እኮ ነው›

እናቴ ዝም አለች..አባቴ የጥያቄዎቻችን መልስ ነው። አባቴን ጠይቀነው መልስ አጥቶ አያውቅም። አባቴ መልስ የሚያጣው ከታናሽ እህቴ ጋር ሲነጋገር ነው።

‹በዚሁ ከከጠሉ እንኳልን..የአለም ፍጻሜ በነሱ በኩል እንዳይመጣ እፈራለው›

‹ውይ.. በስመአም በወልድ! ምን እያልክ ነው? ስንት ጥሩ የሚወራ እያለ..ምነው ቢራራ?› እናቴ ለማልቀስ በቃጣው ድምጽ ከወደ ጓዳ ምሬቷን ገለጸች። ይሄን የድንጋጤ ድምጽ ያወጣው ፊቷ ምን እንደሚመስል ለማሰብ አልተቸገርኩም፡ እናቴ ሁልጊዜ ስለ መጥፎ ነገር ሲነሳ ፊቷን በፍራቻ የመዘፍዘፍ ልማድ አለባት።

‹እውነቴን እኮ ነው..ጦርነቱ ወደ ኒውክሌር ጦርነት እያዘገመ ነው›

‹ታዲያ የሆነ እንደሆነስ! እንዴት ሆኖ ነው የአለም ፍጻሜን የሚያመጣው?

‹ኒውክሌር ማለት አለምን የሚያጠፋ መሳሪያ ነው..› ብሎ አባቴ ዝም አለ።

‹አበስ ገበርኩ› እያለች እናቴ ከጓዳ ወጣች። አለም አሁን የምትጠፋ ይመስል ሳሎኑ መሀል ላይ ቆማ እኔንም አባቴንም ታናሽ እህቴንም በአንድ ጊዜ አስተዋለችን። በእናት አይን፣ ሶስት ሰው በአንድ ጊዜ ሲታይ የመጀመሪያዬ ነው። ሶስት ሰው በአንድ አይን ማየት እንዴት ቻለችበት? እያልኩ እስከዛሬ ባላስተዋልኩት በእናቴ ብቃት እየተደነኩ ባለበት ሰዐት የታናሽ እህቴን ድምጽ ሰማሁት።

**‹ግን ስምንድነው የሚጣሉት?**

‹ዩክሬን የናቶ አባል ካልሆንኩ ብላ› አባቴ መለሰ።

‹ብቶን ምን ችግር አለው? እህቴ ጠየቀች።

‹ከሆነች የሩሲያን ደህንነት፣ ኃያልነት ባጠቃላይ ሉአላዊ ጥያቄ ውስጥ ይከተዋል› ሲል መለሰላት። ይግባት አይግባት እንጃ አፏን ከፍታ ሌላ ጥያቄ ስታምጥ ትታየኛለች።

**‹ስምንድነው የሚከተው?**

‹ምክንያቱም አለም የራስ ወዳዶች ቤት ስለሆነች። ሁሉም ለሌሎች እንድትመች ሳይሆን ለራሱ እንድትመቸው አድርጎ እየጠፈጠፋት ነው። ይሄ የኃይል ሚዛን ደግሞ ድሀውን እየጨቆነው ነው። ዝሆኖች ሲጣሉ ሳሩ ነው የሚጎዳው። የዝሆኖች ጥል ዝሆኖችን ጎድቶ አያውቅም። በእኛም አገር እንዲሁ ነው..

**‹ዝሆኖቹ እነማናቸው?**

አባቴ እህቴን ከዚህ በላይ ሊያስረዳት አልፈለገም። ሁልጊዜ የእህቴ ጥያቄ የአባቴ መቆሚያ ነው። እኛ ቤት ውስጥ አባቴ በእህቴ፣ እህቴም በአባቴ ግራ እንደተጋቡ ነው።

እናቴ ብዙ ቆማ ወደ ጓዳ አዘገመች። ለምን እንደምትሰጋ አላውቅም ጦርነት አትወድም፣ ክፉ ነገር መስማት ያስጨንቃታል። ከአባቴ ንግግር በኋላ አላረፈችም። ቀን ሙሉ እዬዬ ስትል ነው የዋለችው። ‹እግዚኦ› ስትል እንኳን ከሀምሳ ጊዜ በላይ ሰምቻታለው። አባቴ የእናቴ የሙሴ ህግ ነው። የኖረችው እየሰማችውና እያደመጠችው ነው። የአለም ሁሉ ጌታ እግዜርን እንኳን የአባቴን ያክል አታምነውም።

አባቴ ቻናል እየቀያየረ ዜና ፍለጋ ወዲያ ወዲህ ሲል ጥዬው ወደ ውጪ ወጣሁ። ማታ ለመኝታ ወደ ቤት ስገባ አባቴን እዛው ሶፋ ላይ ስለ ሩሲያና ዩክሬን ዜና እየሰማ አገኘሁት። አስቸኩሎ ያስሮጠኝን የጋሽ ቢራራን መልዕክት ሳልነግረው እንደያዝኩት ተኛሁ። ጠዋት ከእንቅልፌ ነቅቼ አይኔን እያሻሸሁ ወደ ሳሎን ስገባ አባቴ የጠዋቱን ዜና ጓጉቶ እየጠበቀ አገኘሁት። ሁላችንም ጸጥ።

# ዓለም አቀፍ



## አምባሳደር ማይክ ሃመር የአሜሪካ የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ ሆነው ተመደቡ

አዲስ አበባ፣ አምባሳደር ማይክ ሃመር የአሜሪካ የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ ሆነው ተመደቡ።

ይህን ተከትሎም ከዚህ ቀደም የአሜሪካ የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ የነበሩትን አምባሳደር ዴቪድ ስታተርፊልድ ተክተው እንደሚሰሩ የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን በትዊተር ገጻቸው አስታውቀዋል።

ሚኒስትሩ አሜሪካ በቀጠናው የምታደርገውን ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ለማስቀጠል ከአዲሱ ልዩ መልዕክተኛ ጋር በጋራ ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውንም ገልጸዋል።



## አሜሪካ ለዩክሬን የምታደርገው የጦር መሳሪያ ድጋፍ ‹በእሳት ላይ ቤንዚን› እንደመጨመር ነው - ሩሲያ

አዲስ አበባ፣ አሜሪካ ለዩክሬን በምትሰጠው የጦር መሳሪያ እርዳታ ‘በእሳት ላይ ቤንዚን’ እየጨመረች ነው ስትል ሩሲያ የአሜሪካን ድርጊት አወገዘች።

አሜሪካ ለዩክሬን የተራቀቁ ሚሳኤሎችን ለማቅረብ ማቀዷ ሆን ብላ ግጭቱ ወደ አልተገባ ደረጃ እንዲያድግ መፈለጓን ያሳያል ሲሉ የክሬምሊን ቃል አቀባይ ዲሚትሪ ፔስኮቭ ተናግረዋል።

የሩሲያው ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰርጌይ ርያብኮቭ በበኩላቸው፥ አሜሪካ አዲሶቹን የሚሳኤል ጦር መሳሪያዎች ለዩክሬን ለማቅረብ ማቀዷ ከሩሲያ ጋር ቀጥተኛ ግጭት ውስጥ ሊከት የሚችል አደጋ እንደሚያስከትል ተናግረዋል።

የአውሮፓ ኅብረት በቀጣይ ሊያደርገው ያሰበውን የኃይል ማዕቀብ በተመለከተም፥ ማእቀቡ ሩሲያን ጨምሮ ለአውሮፓ አገራት፥ ለአሜሪካ እና ለመላው የሃይል ገበያ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠሩ አይቀርም ብለዋል።

በሩሲያ በኩል ጉዳቱን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስራዎች እየተሰሩ ነው ማለታቸውንም ቲአርቲ ዘግቧል።

ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ትናንት በኒውዮርክ ታይምስ በታተመ ጸሁፍ ላይ፥ አሜሪካ ልህቀት ያላቸው ዘመናዊ የሮኬት መሳሪያዎችን ለዩክሬን ታቀርባለች ማለታቸው የተዘገበ ሲሆን ዋሽንግተን በርካታ የሮኬት ማስወንጨፊያዎችንም ለዩክሬን ለመላክ መስማማቷን በርካታ የዓለም መገናኛ ብዙኃን መዘገባቸው ይታወሳል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የሀትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ቁብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# ዓርብ አዲስ ዘመን ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## ሉሲዎቹ የሴካፋን ጉዞ በጣፋጭ ድል ጀምረዋል

**ቦጋለ አበበ**

በዩጋንዳ አስተናጋጅነት ከትናንት በስቲያ የተጀመረው የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ (ሴካፋ) የሴቶች ዋንጫ በተለያዩ ጨዋታዎች ቀጥሏል። በውድድሩ ለመሳተፍ ከቀናት በፊት ወደ ዩጋንዳ ያቀኑት የኢትዮጵያ ሴቶች ብሔራዊ ቡድን (ሉሲዎቹ) ትናንት የመጀመሪያ ጨዋታቸውን አከናውነዋል። ሉሲዎቹ ዛንዚባርን በመግጠም አምስት ለዜሮ በሆነ ሰፊ ውጤት በማሸነፍ የሴካፋ ዋንጫ ጉዟቸውን በጣፋጭ ድል ጀምረዋል።

ገና ጨዋታው በተጀመረ አንደኛው ደቂቃ ላይ በአረጋሽ ካልሳ ግብ መምራት የቻሉት ሉሲዎቹ በሃያ ሰባተኛና ሃምሳ ሰባተኛ ደቂቃ ላይ አምበሏና የግብ ቀበኛዋ የሉሲዎቹ የአጥቂ መስመር ተጫዋች ሎዛ አበራ ባስቆጠረቻቸው ሁለት ግቦች መሪነታቸውን ማጠናከር ችለዋል። በሰባ አራተኛውና በሰማንያ ስምንተኛው ደቂቃ ላይም ቅድስት ዘለቀ ሁለት ግቦችን አክላ ሉሲዎቹ ጨዋታውን በቀላሉ ተቆጣጥረው የሚፈልጉትን ውጤት ይዘው ሊወጡ ችለዋል።

የሉሲዎቹን ተተኪዎች የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ሴቶች ብሔራዊ ቡድን በመምራት ስኬታማ ጊዜን ያሳለፉት አዲሱ የሉሲዎቹ አሰልጣኝ ፍሬው ኃይለገብርኤል በዋናው ብሔራዊ ቡድንም የመጀመሪያ ጨዋታቸውን በድል መጀመር ችለዋል። ከበርካታ ወራት በፊት የወጣቶቹን ብሔራዊ ቡድን እየመሩ በ20 ዓመት በታች የሴካፋ ዋንጫ የውድድሩ አስተናጋጅ የነበረችውን ዩጋንዳን በፍጻሜ ጨዋታ በመርታት በኢትዮጵያ ሴቶች እግር ኳስ ታሪክ ትልቅ የሆነውን ዋንጫ ማንሳት የቻሉት አሰልጣኝ ፍሬው በሴካፋ በርካታ ግብ የሚያስቆጥርና ጥቂት ግቦች ብቻ የሚያስተናግድ ጠንካራ ቡድን መስርተው አሳይተዋል። ከሴካፋው ጣፋጭ ድል በኋላም ያንኑ ቡድን እየመሩ በዓለም ከ20 አመት በታች ዋንጫ የማጣሪያ ጨዋታ እስከ መጨረሻውና አራተኛው ዙር መጓዛቸው ይታወሳል።



ሉሲዎቹ በሴካፋ ዋንጫ የመጀመሪያ ጨዋታቸው ዛንዚባርን 5ለ0 መርታት ችለዋል፣

አሰልጣኙ በወጣቶች ቡድን ያስመዘገቡት ውጤት በዋናው ብሔራዊ ቡድንም ተመሳሳይ ስኬት ለማስመዝገብ ተስፋ እንዲጣልባቸው አድርጓል። ለዚህም ከሳምንታት በፊት ሉሲዎቹን በዋና አሰልጣኝነት ለመምራት ኃላፊነቱ ሲሰጣቸው የቡድን ስብስባቸውን ስኬታማ ከነበረው የ20 አመት በታች ቡድን በርካታ ወጣት ተጫዋቾችን በማሳደግ ከነባሮቹና ልምድ ካካበቱት ጋር በማጣመር ሲዘጋጁ ቆይተዋል። በአጭር ጊዜ ዝግጅት ያዋሃዱት ቡድንም የመጀመሪያ ፍልሚያውን ትናንት በድል በመወጣት ፍሬውን አሳይቷቸዋል።

አሰልጣኝ ፍሬው በወጣቶቹ ቡድን በርካታ ግብ የሚያስቆጥር በአንጻሩ ትንሽ ግብ የሚቆጠርበት ጠንካራ የአጥቂና የተከላካይ መስመር ያለው ቡድን መስራት እንደሚችሉ አሳይተዋል። በዋናው ቡድንም ትናንት የተጋጣሚያቸው ዛንዚባር ብሔራዊ ቡድን ደካማነት እንዳለ ሆኖ ገና በመጀመሪያ ጨዋታቸው አምስት ግብ አስቆጥረው ምንም ግብ ሳይቆጠርባቸው ማሸነፍ መቻላቸው ገና ተገንብቶ ያላለቀው ቡድናቸው ተስፋ እንዲጣልበት አድርጓል።

በውድድሩ በምድብ ሁለት ከታንዛኒያ፣ ዛንዚባር እና ደቡብ ሱዳን ጋር የተደለደሉት ሉሲዎቹ ትናንት ያስመዘገቡት ድልና ያሳዩት እንቅስቃሴ ከቀጣይ ተጋጣሚዎቻቸው አቅም አኳያ ወደ ጥሎ ማለፍ ፍልሚያ ያልፋሉ ተብለው ከሚጠበቁ ቡድኖች አንዱ አድርጓቸዋል። ያምሆኖ በጥሎ ማለፍ ዙሩ ሊገጥሟቸው የሚችሉ ቡድኖች ጥንካሬ ሉሲዎቹ በውድድሩ ለመቆየት የሚያደርጉትን ፍልሚያ ቀላል እንደማያደርገው ይጠበቃል።

ስምንት አገራት በሁለት ምድብ ተከፍለው በሚፋለሙበት የዘንድሮው የሴካፋ ሴቶች ዋንጫ በሁለኛው ምድብ አዘጋጇ ዩጋንዳ፣ ቡሩንዲ፣ ርዋንዳ እና ጅቡቲ ተደልድለዋል። ዩጋንዳ በውድድሩ መክፈቻ እለት ርዋንዳን ሁለት ለምንም መርታቷ የሚታወስ ሲሆን ሁለተኛው ጨዋታ ቡሩንዲ ጅቡቲን ሶስት ለዜሮ በመርታት ተደምድሟል።

ለአምስተኛ ጊዜ እየተካሄደ የሚገኘው የሴካፋ ሴቶች ዋንጫ ባለፈው ዓመት በጅቡቲ አስተናጋጅነት ሊካሄድ ቀጠሮ ተይዞለት የነበረ ሲሆን ውድድሩ ሲቃረብ ጅቡቲ ጨዋታዎችን የምታስተናግድበት ኤል ሃጅ ሃሰን ጉሌድ አፕቲዶን ስቴድየም ግንባታ ባለመጠናቀቁ አዘጋጅነቷን ማንሳቷ ይታወሳል። በዚህ የሴካፋ ሴቶች ዋንጫ ያለፈው ውድድር አሸናፊ የሆነችውን ኬንያን ጨምሮ ሌሎች ጠንካራ አገራት አለመሳተፋቸው ይታወቃል።

## ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ
### ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም



የኢ.ፌ.ዴ.ሪ
ሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጽ/ቤት
አድራሻ፡-

አዲስ አበባ
አራዳ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 1
ፒያሳ-ከአራዳ ህንፃ ጎን፣ እየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት ህንፃ ላይ

የስልክ ቁጥሮች

ጽ/ቤት፡- 011-1-11 68 88
የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር፡- 011-1-56 22 89 ወይም 011-1-11 66 79
ኮሙኒኬሽን፡- 011-1-26 67 24
ነፃ የስልክ መስመር፡- 6939

ፋክስ
011-1-116886
ፖስታ ሳ.ቁ
22627
ኢ-ሜይል
constitutionalinquiry.et@gmail.com
ፌስቡክ ገፅ
https://www.facebook.com/CCIFDRE/
ድረ-ገፅ
www.cci.gov.et

### የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84

1. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል። በሚያደርገው ማጣራት መሰረት ሕገ መንግሥቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል።

2. በፌዴራል መንግሥትም ሆነ በክልል ሕግ አውጪ አካላት የሚወጡ ሕጎች ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ ሲነሳና ጉዳዩ በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለ ጉዳዩ ሲቀርብለት መርምሮ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል።

3. በፍርድ ቤቶች የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ ሀ/ ሕገ መንግሥቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይመልሳል በአጣሪ ጉባዔው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለጉዳይ ቅሬታውን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በይግባኝ ማቅረብ ይችላል። ለ/ የትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ለመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል።

4. የሚመራበትን ስነ ሥርዓት አርቅቆ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ